## ምዕራፍ ፣ ፲፫ ፣ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ስለ ፡ መንከራተታቸው ።

፩ ፣ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ግብፅ ፡ ወርዶ ፡ ከተቀመጠ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ ልጆቹ ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ በፍጥነት ፡ እየበዙ ተራቡ ። ዕብራውያን ፡ ግብፅን ፡ በለቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ አያንስም ፡ ነበር ። መሪያቸው ፡ ሙሴም ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ሆኖት ፡ ነበር ። ባካሄዱ ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ምንም ፡ የዋህና ፡ ትሑት ፡ ቢሆን ፡ ታላቅ ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ የመላበት ፡ ትክክለኛ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

፪ ፣ የዕብራውያን ፡ ዐሳባቸው ፡ ከግብፅ ፡ ተነሥተው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ለመድረስ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ የቀድሞ ፡ አገራቸው ፡ ዛሬ ፡ ፍልስጥኤም ፡ ጳለስታይን ፡ ወይም ፡ ጳለስቲና ፡ ይባላል ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደዚያ ፡ ለመድረስ ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ በኩል ፡ ማለፍ ፡ ነበረባቸው ።

፫ ፣ መንገዱን ፡ ስተው ፡ እንዳይባዝኑ ፡ በሚጓዙበት ፡ መንገድ ፡ ደመናው ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ ሆኖ ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ በፊታቸው ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ። ሌሊትም ፡ የደመናው ፡ ምሰሶ ፡ ተለውጦ ፡ የእሳት ፡ ምሰሶ ፡ እየሆነ ፡ በሚጓዙበት ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ያበራላቸው ፡ ነበር ።

፬ ፣ የአገሩ ፡ አውራጃ ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ ያልኖረበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ውኃ ፡ አይገኝበትም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ መና ፡ ድርጭትም ፡ እየሰጠ ፡ መገባቸው ። ውኃም ፡ በተጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ዐለቱን ፡ ቢመታው ፡ ውኃ ፡ በብዙ ፡ ተንዶለዶለላቸው ። አየሩ ፡ በዚያ ፡ ያለልክ ፡ ሙቀት ፡ ነበረና ፡ ይህ ፡ ታላቅ ማዳን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ዕብራውያን ፡ አማሌቃውያንን ፡ ለመምታት ፡ መንፈሳዊ ፡ ርዳታ ፡ ስለ ፡ አገኙ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ቻሉ ።

፭ ፣ ነገር ፡ ግን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ምንም ፡ ብዙ ፡ ምሕረት ፡ ቢደረግላቸው ፡ እነርሱ ፡ ምስጋና ፡ የሌላቸው ፡ ዐመፀኞች ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛውን ፡ አምላክ ፡ ትተው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ያዞሩ ፡ ነበር ።

፮ ፣ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ለሙሴ ፡ በተገለጠበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ የምናመልከው ፡ የወርቅ ፡ ጥጃ ፡ ሥራልን ፡ ብለው ፡ አሮንን ፡ አስገደዱት ፣ ከምስር ፡ ምድር ፡ ያወጣቸውን ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ የሆዋን ፡ ትተው ፡ ለዚህ ፡ ለምናምንቴ ፡ ጣዖት ፡ ተንበረከኩ ።

፯ ፣ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያል ምሕረት ፡ ቀጣቸው ። ብዙዎች ፡ በመቅሠፍት ፡ ተቀሠፉ ። እኩሌቶችንም ፡ ምድር ፡ ዋጠቻቸው ። የተረፉትም ፡ ከግብፅ ፡ እስከ ፡ ከነዓን ፡ ቅርብነቱ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡

አምሳ ፡ ማይል ፡ በሚሆን ፡ በምሥራቅ ፡ አገር ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ መን
ከራተት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ።

፰ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ሳይደርሱ ፡ ብዙዎቹ ፡ ከግብፅ ፡ ሸሽተው ፡ የወጡት ፡ በመ
ንገድ ፡ ሳሉ ፡ አለቁ ። ልጆቻቸው ፡ ተልፋ ፡ የተሰጣቸውን ፡ አገር ፡ ወረሱ ፡ እንጂ
እነሱ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በረሃ ፡ በአሸዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብረው ፡ ቀሩ ። ፒስጋ ፡
በሚባል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የተሰጠችውን ፡ አገር ፡ እንዲያይ ፡ የተፈቀደለት ፡
ሙሴ ፡ እንኳ ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመቱ ፡ እዚያው ፡ ሞተ ።

፱ ፡ ሙሴ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የእስራኤላውያን ፡ መሪ ፡ ሆነ ።
በርሱ ፡ መሪነት ፡ ተስፋ ፡ ወደ ፡ ተሰጣቸው ፡ አገር ፡ ገቡና ፡ በአገሪቱ ፡ የተገኙትን ፡
ሕዝብ ፡ አስገበሩዋቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የከነዓን ፡ አገር ፡ ላሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡
እስራኤል ፡ ተከፈለች ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ያዕቆብ ፡ በግብፅ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ዘመን ፡ እንሥቶ ፡ እስራኤል ፡ ከግ
ብፅ ፡ እስከ ፡ ወጡበት ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ፡ ?
በዚህ ፡ ዘመን ፡ የእስራኤል ፡ ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡ ያህል ፡ ኑሩዋል ፡ ?
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ዕድሜው ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ኑሩዋል ፡ ?
ባካሄዱ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ኑሩዋል ፡ ?

፪ ፡ ከነዓን ፡ ከግብፅ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
በከነዓንና ፡ በግብፅ ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
ዕብራውያን ፡ ሲንከራተቱ ፡ የኖሩት ፡ በየትኛው ፡ አገር ፡ ነው ፡ ?

፫ ፡ ዕብራውያን ፡ በምን ፡ ተመሩ ፡ ?

፬ ፡ የተጓዙት ፡ በንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ይመገቡ ፡ ኑሩዋል ፡ ?
ምንጭ ፡ ወይም ፡ ፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ባላገኙ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ይሆኑ ፡ ነበር ፡ ?
ስለምን ፡ ውኃ ፡ አስፈለጋቸው ፡ ?

፭ ፡ ዕብራውያን ፡ ለተደረገላቸው ፡ የምሕረት ፡ ሥራ ፡ ምስጋና ፡ ኖሮዋ
ቸዋልን ፡ ?

፮ ፡ ሙሴ ፡ ወደ ፡ ሲና ፡ ተራራ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
እግዚአብሔርን ፡ ከማምለክ ፡ ይልቅ ፡ ለጥጃ ፡ ምስል ፡ መስገዳቸው ፡
ዕብራውያንን ፡ ሰነፎችና ፡ ከፉዎች ፡ አያሰኛቸውምን ፡ ?
ልጆች ፡ ላባትና ፡ ለናታቸው ፡ ታዘው ፡ የሚገባቸውን ፡ ሳያደርጉ ፡
የራሳቸውን ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ ቢከተሉ ፡ እንደ ፡ ዕብራውን ፡ መሆናቸው ፡
አይደለምን ፡ ?

፯ ፡ በማይታዘዙ ፡ ዕብራውያን ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መጣባቸው ፡ ?
መቸውንም ፡ ሁልጊዜ ፡ አለመታዘዝን ፡ ቅጣት ፡ እንዲከተለው ፡ አታውቅምን ፡ ?
ዕብራውያን ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዞሩ ፡ ?
ከግብፅ ፡ እስከ ፡ ከነዓን ፡ ርቀቱ ፡ የቱን ፡ ያህላል ፡ ?
ከግብፅ ፡ ከወጡት ፡ ዕብራውያን ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ የገቡት ፡ የሚበዙት ፡ ናቸውን ፡ ?
ሙሴ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ከነዓን ፡ ለስንት ፡ ተከፈለ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የሚድን ፡ መኀግሥት ፡ መገለባበጥ ።
### ዕምዕንና ፡ መሳፍንቱ ።

፩ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በከነዓን ፡ ገብተው ፡ ከተደላደሉ ፡ በኋላ ፡ በመሳፍንት ፡ ተገዙ ። እነዚህም ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ገገሮች ፡ በጦርም ፡ ጊዜ ፡ አዝማቾች ፡ ነበሩ ። ከነዚህ ፡ ጥቂቶቹ ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ሆነው ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ሠርተዋል ።
፪ ፡ ያንደኛው ፡ ስም ፡ ጌዴዎን ፡ ነው ። እሱም ፡ እስራኤልን ፡ በሚዳኝበት ፡ ዘመን ፡ የሚዶናውያን ፡ ጦር ፡ አገሩን ፡ ወረረው ። ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ተጭኖ ፡ ገዝቶታል ። እስራኤልን ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ የሚያድንበትን ፡ መንገድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጌዴዎን ፡ አስተማረው ።
፫ ፡ ጌዴዎን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ መረጠና ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የሸክላ ፡ ማሰሮ ፡ እንዲይዙ ፡ መብራትም ፡ እንዲያደርጉበት ፡ አዘዛቸው ። እነዚህን ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ሚዶናውያን ፡ ሰፈር ፡ ገባ ። ተሸንፈው ፡ የሚኖሩት ፡ እስራኤላውያን ፡ ወደ ፡ ሰፈራችን ፡ ይገባሉ ፡ ብለው ፡ ትንሽ ፡ እንኳን ፡ ሳይጠረጠሩ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ሥራዊት ፡ በየድንኳኑ ፡ ሁሉንም ፡ እንቅልፍ ፡ ገርግዞት ፡ ተጋድሞ ፡ ነበር ።
፬ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ጥፋታቸው ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፡ ጌዴዎን ፡ ለሰዎቹ ፡ ምልክት ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ ማሰሮዋቸውን ፡ ሰበሩና ፡ ወዲያው ፡ የያዙትን ፡ መለከታቸውን ፡ እየነፉ ፡ አደባለቁት ። በዚህ ፡ በሚያስፈራ ፡ ጩኸትና ፡ ድብልቅልቅ ፡ የሚዶን ፡ ሰዎች ፡ ከእንቅልፋቸው ፡ ነቁ ።
፭ ፡ በድብልቅልቁና ፡ በመለከቱ ፡ ጩኸት ፡ መኻከል ፡ እስራኤላውያን ፡ « የእግዚአብሔርና ፡ የጌዴዎን ፡ ሰይፍ ፡ » እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡

በሚዶን ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ ወደቀባቸው ። ያለጥርጥር ፡ በጠቅላላው ፡ የዕብራውያን ፡ ጦር ፡ ሰብሮ ፡ እሰፈራችን ፡ ገብቷል ፡ ብለው ፡ ዐሰቡ ። በሰፈራቸውም ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ መሰላቸው ።

፯ ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የገዛ ፡ ባልንጀራውን ፡ ጠላት ፡ መስሎት ፡ እያሳሳተ ፡ ይጨረግደው ፡ ጀመር ። ስለዚህ ፡ የሚዶን ፡ ሰዎች ፡ የተላለቁት ፡ ከእስራኤል ፡ ሰይፍ ፡ ይልቅ ፡ በገዛ ፡ ሰይፋቸው ፡ ነው ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ በታላቅ ፡ ርዳታ ፡ አዳናቸው ።

፰ ፤ ከእስራኤል ፡ መሳፍንት ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የነበረው ፡ ሶምሶን ፡ ይባላል ። እንደ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ ኀይለኛ ፡ ከቶ ፡ በዓለም ፡ አልተገኘም ፤ እጅግ ፡ የሚያስገርመው ፡ ኀይሉ ፡ በራሱ ፡ ጠጕር ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

፱ ፤ ጠጕሩን ፡ ያሳድግና ፡ ወርዶ ፡ በንገቱ ፡ ላይ ፡ የጋሸበ ፡ ጤፍ ፡ መስሎ ፡ ሲጐናበልለት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡ ሰው ፡ ያህል ፡ ኀይል ፡ ያገኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጠጕሩን ፡ በቈረጠ ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ ኀይል ፡ አያገኝም ።

፲ ፤ በሶምሶን ፡ ዘመን ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ እስራኤልን ፡ አጥቅተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ አጠቋቸው ፡ ሶምሶን ፡ አይወዳቸውም ፡ ነበረና ፡ ባለው ፡ ኀይል ፡ ሁሉ ፡ ሊጐዳቸው ፡ ዐሰበ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዕብራውያን ፡ በከነዓን ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ አገዛዛቸው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? መሳፍንቱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? ጌዴዎን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፪ ፤ ጌዴዎን ፡ የሚዶንን ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ድል ፡ አደረጋቸው ፡ ? ንገር ።

፫ ፤ ሶምሶን ፡ እንዴት ፡ አደረገ ፡ ?

፬ ፤ ኀይል ፡ ያገኘበት ፡ ምክንያት ፡ በምንድነው ፡ ?

፭ ፤ ፍልስጥኤማውያን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? ሶምሶን ፡ ለምን ፡ ጠላቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ሶምሶን ፡ በፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሠራውና ፡ የሞተበት ፡ ምክንያት ።

፩ ፤ ሶምሶን ፡ ከአህያ ፡ መንጋጋ ፡ በቀር ፡ በእጁ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሳይኖረው ፡ ባንድ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍሮች ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ገድሎአል ። ዳግም ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ጋዛ ፡ በምትባል ፡ ከተማቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ በዘጉበት ፡ ጊዜ ፡ የከተማውን ፡ መዝጊያዎች ፡ እንዳለ ፡ በትከሻው ፡ ተሸክሞ ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ ጥሎታል ።

፩ ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ ሶምሶን ፣ ምንም ፣ ፍልስጥኤማውያንን ፣ ቢጠላቸውና ፣ ክፉት ፣ ነገ
ርም ፣ ቢሠራባቸው ፣ ከውስጣቸው ፣ አንዲት ፣ የሚወዳት ፣ ሴት ፣ ነበረችው ።
ስምዋም ፣ ዳሊላ ፣ ትባላለች ። እሱዋም ፣ በበኩልዋ ፣ ወደድሁህ ፣ እያለች ፣ ታቂላ
ምጠው ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ዋና ፣ ዐሳቡዋ ፣ ልታጠፋው ፣ ፈልጋ ፣ ነው ።
፪ ፤ ይህቺው ፣ ሴት ፣ ከሌላው ፣ ሁሉ ፣ ይልቅ ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ ኀይል ፣ ያገኘበትን ፣
ምክንያት ፣ እንዲነግራት ፣ ታባብለው ፣ ነበር ። ሶምሶን ፣ መጀመሪያ ፣ አታለላት ።
በሰባት ፣ ባልደረቀ ፣ በርጥብ ፣ ጠፍር ፣ ወይም ፣ ባዲስ ፣ ገመድ ፣ ብታሰር ፣ እንደ
ሌላው ፣ ሁሉ ፣ እደክማለሁ ፣ አላት ።
፫ ፤ እንዲሁም ፣ ዳሊላ ፣ በሰባት ፣ ርጥብ ፣ ጠፍርና ፣ ባዲስ ፣ ገመድ ፣ አሰረችው ።
ነገር ፣ ግን ፣ ሶምሶን ፣ ርጥቡን ፣ ጠፍር ፣ አዲሱንም ፣ ገመድ ፣ እንደ ፣ ክር ፣ በጣ
ጠሰው ፤ በመጨረሻው ፣ ዳሊላ ፣ አሸነፈችውና ፣ በእውነት ፣ ኀይሉ ፣ የሚደክም
በትን ፣ ምክንያት ፣ እውነቱን ፣ ነገራት ።
፬ ፤ ሚስጢሩን ፣ ካወቀች ፣ በኋላ ፣ እንቅልፍ ፣ ወስዶት ፣ ሳለ ፣ ጠጕሩን ፣ ቈረጠችው ።
ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ለወገኖችዋ ፣ ለፍልስጥኤም ፣ ሰዎች ፣ ያውላችሁ ፣ አለቻቸው ። እነ
ሱም ፣ ይዘው ፣ ዐይኑን ፣ አወለቁት ፤ በእግር ፣ ብረትም ፣ አሰሩት ። በእስር ፣ ቤትም ፣
ሳለ ፣ እንደ ፣ እንስሳ ፣ ያሠሩት ፣ ነበር ።
፭ ፤ ሶምሶን ፣ በሥራ ፣ እጅግ ፣ ይደክም ፣ ነበር ። ጠጕሩ ፣ እያደረ ፣ እያቀመቀመ ፣
ሲያድግለት ፣ ጊዜ ፣ ኀይል ፣ ይሰማው ፣ ጀመር ። እንደ ፣ ገና ፣ ኀይለኝነቱ ፣ በምድር ፣
ላይ ፣ ታወቀለት ።
፮ ፤ አንድ ፣ ቀን ፣ ፍልስጥኤማውያን ፣ ዳጎን ፣ ለሚሉት ፣ ጣዖታቸው ፣ በዓል ፣ አድ
ርገው ፣ እጅግ ፣ ደስ ፣ ብሏቸው ፣ ሳለ ፣ ያለ ፣ ልክ ፣ ፈንድቀው ፣ ደስታቸው ፣ ስለ
በዛ ፣ እስኪ ፣ ሶምሶን ፣ ይጠራና ፣ የሚያስገርመውን ፣ ኀይሉን ፣ እያሳየ ፣ በመኻከላ
ችን ፣ እየተወዛወዘ ፣ ይዝፈንልን ፣ አሉ ።
፯ ፤ ሶምሶንን ፣ ተእስር ፣ ቤት ፣ ጠርተው ፣ ወደ ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ እየመሩ ፣ አገቡት ።
የታሰረበት ፣ የእግር ፣ ብረት ፣ በተራመደ ፣ ቍጥር ፣ ይቅጨለጨል ፣ ነበር ። ዕውር ፣
ሆኖ ፣ የሚያሳዝን ፣ ሰው ፣ ይመስል ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ጠጕሩ ፣ አድጎለት ፣
በትከሻው ፣ ላይ ፣ ጐፍለል ፣ ብሎ ፣ ነበር ።
፰ ፤ ሶምሶን ፣ የሚያስደንቀውን ፣ የኀይሉን ፣ ነገር ፣ እያሳየ ፣ ካጫወታቸው ፣ በኋላ ፣
በምሰሶውና ፣ በምሰሶ ፣ መኻከል ፣ ጥቂት ፣ ዕረፍት ፣ እንዲያገኝ ፣ ለመነ ። በቤቱ ፣
ውስጥ ፣ በላይም ፣ በታችም ፣ የፍልስጥኤም ፣ ሰዎች ፣ ጥቅጥቅ ፣ ብለው ፣ እየተጋፉ ፣
ቤቱን ፣ መልተውት ፣ ነበር ።
፱ ፤ ተእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ የሚጐዳቸው ፣ አልመሰላቸውምና ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ኀይለኛ ፣
ኖሮአል ፣ እያሉ ፣ በመደነቅ ፣ ሳሉ ፣ ኀይለኛው ፣ ሰውዬ ፣ እጁን ፣ ዘረጋና ፣ በጐኑና ፣
በጐኑ ፣ ያለውን ፣ የቤቱን ፣ ምሰሶ ፣ በነቀነቀው ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ ምድር ፣ መናወጥ ፣
ቤተ ፣ ጣዖቱ ፣ ተንቀጠቀጠ ። ወዲያው ፣ ሶምሶን ፣ ጐንበስ ፣ ብሎ ፣ ባለ ፣ ኀይሉ ፣

ምሰሶውን ፡ በማታው ፡ ጊዜ ፡ ቤቱ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ተንዶ ፡ ሲወድቅ ፡ የነ
ጐድጓድ ፡ ድምጽ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እዚያው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡
እነዚያ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሁሉ ፡ ተደፍነው ፡ ቀሩ ። ሶምሶንም ፡ አብሮ ፡
ጠፋ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሞቱ ፡ ጠላቶቹን ፡ ድል ፡ በማድረጉ ፡ ደስ ፡ እንዳለው ፡
ይታያል ። እርሱም ፡ ከክቡራኑና ፡ ከኀያላኑ ፡ ሬሳ ጋር ፡ በውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ ቀረ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ሶምሶን ፡ የፍልስጥኤምን ፡ ሰዎች ፡ የመታው ፡ በምን ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፡ የጋዛን ፡ ከተማ ፡ በር ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ሰበረው ፡ ?
ዳሊላ ፡ የተባለችው ፡ ማነች ፡ ?
፫ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ሶምሶን ፡ እርሱዋን ፡ ( አሞኛት ፡ ) አታለላት ፡ ?
፬ ፡ ዳሊላ ፡ የሶምሶንን ፡ ኀይል ፡ የቀነሰችበት ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ነው ፡ ?
ፍልስጥኤማውያን ፡ ሶምሶንን ፡ ምን ፡ አደረጉት ፡ ?
፭ ፡ የሶምሶን ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ካደገለት ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፮ ፡ ሶምሶን ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ የጣዖት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡
እንዳፈራረሰው ፡ ታሪኩን ፡ ንገረን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የሳኦል ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ።

፩ ፡ ሙሴ ፡ ዕብራውያንን ፡ ከግብፅ ፡ ካወጣበት ፡ ጀምሮ ፡ ፬አራት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ እስ
ኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ አያሎች ፡ ገዦች ፡ በሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ላይ ፡ ገዝተዋል ። ነገር ፡
ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ሕዝቡ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አገዛዝ ፡ በመገዛታቸው ፡
ደስታ ፡ አልነበራቸውምና ፡ ምኞታቸው ፡ በላያቸው ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ነግሦ ፡
እንዲገዛቸው ፡ ነበር ።
፪ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ገዢ ፡ የነበረው ፡ ሳሙኤል ፡ ሽምግሎ ፡ ነበር ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ብልህ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ካገኘው ፡ ዕው
ቀት ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ አግኝቶ ፡ ነበር ።
፫ ፡ ሕዝቡ ፡ ንጉሥ ፡ ያስፈልገናል ፡ ቢሉ ፡ ሳሙኤል ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ብትኖሩ ፡
ይሻላችሁ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለንጉሥ ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባቸውን ፡ ንጉሥም ፡ ከነ
ርሱ ፡ የሚፈልግባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው ።

፬ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እስራኤል ፡ ሳሙኤል ፡ የነገራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሳይሰሙ ፡ አሁንም፡ ንጉሥ ፡ እንፈልጋለን ፡ አሉ ፤ የሚፈልጉትም ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ በደኅና ፡ የሚገዛቸው ፤ በጦርም ፡ ጊዜ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ የሚዋጋላቸው ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ሳሙኤልም ፡ ለእስራኤል ፤ ንጉሥ፡እንዲያነግሥላቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር፡ አመለከተ ። ለንጉሥነትም ፡ የታሰበው ፡ ሳዖል ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ወጣት፡ጐበዝ፡ ነበር ። አባቱም ፡ ቂስ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ እጅግ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ነበር ። ቁመቱም፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘለግ ፡ ያለው ፡ ነው ። ሳሙኤልም፡ቅብዐ ፡ መንግሥት፡ ቀባውና ፡ እነሆ ፡ ንጉሣችሁ ፡ ብሎ፡ንጉሥ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ለሕዝበ፡እስራኤል፡ ሰጣቸው ።

፮ ፤ ሳዖል ፡ ንጉሥ፡ለመንግሥቱ ፡ መጀመሪያ፡አስተዋይና ፡ መልካም፡ሰው፡ነበር ። እያደረ ፡ የሳሙኤልን ፡ ምክር ፡ ንቆ፡ለአምላክ ፡ አልታዘዘም ። ሳሙኤልም ፡ በጎውን ፡ ነገር፡ሊያመለክተው ፡ ፈቃዱ ፡ ነበር ።

፯ ፤ በሳዖል ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ እስራኤላውያን ፡ ሁለግዜ፡በዙሪያቸው ፡ ካሉት፡ ሕዝብ ፡ ጋር፡ይዋጉ፡ነበር ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ አገሩን ፡ በወረሩት ፡ ጊዜ ፡ በጦራቸው ፡ ውስጥ ፡ ከጋት ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ጎልያድ ፡ የሚባል ፡ ኀይለኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

፰ ፤ የሱም ፡ ቁመት ፡ ከስድስት ፡ ክንድ ፡ አያንስም፡ነበር ። ከራሱ፡እስከ፡እግሩ፡ የነሐስ ፡ ጥሩር ፡ ደፍቶ ፡ የነሐስም ፡ ጦር ፡ ተሸክሞ ፡ ነበር ። በራሱ ፡ የደፋው ፡ የነሐስ ፡ ጥሩር ፡ ሠላሳ ፡ ፓውንድ ፡ ይመዝን ፡ ነበር ።

፱ ፤ ይህ፡ኀይለኛው ፡ የሚያስፈራ ፡ ሰውዬ ፡ ከፍልስጥኤማውያን፡ሰፈር፡በየቀኑ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ እያንፈራጠጠ ፡ ማነው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚታገል ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የምተመትመው ፡ እኔን ፡ የሚቋቋመኝ ፡ እንዳለ ፡ ይውጣና ፡ ይግጠመኝ ፡ እያለ፡እስራኤልን ፡ ይላገድባቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ አንበሳ ፡ እንዳስደነበራቸው ፡ በጎች ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ አገርግረው ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ምን ፡ ያህል፡ዘመን ፡ ዕብራውያን ፡ በመሳፍንት ፡ ተገዙ ፡ ?
፪ ፤ ሳሙኤል ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፫ ፤ ሕዝቡ ፡ ንጉሥ ፡ እንፈልጋለን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ፡ምን ፡ አላቸው ፡ ?
፬ ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ምን ፡ ዐሰቡ ፡ ?
፭ ፤ ሳዖል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምንስ ፡ አደረገ ፡ ?
፮ ፤ ጎልያድ ፡ ማነው ፡ ? ስለ፡ጎልያድ ፡ ምን ፡ ታውቃለህ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ስለ ፡ ዳዊትና ፡ ስለ ፡ ጎልያድ ፡ መዋጋት ።

፩ ፤ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ እረኛ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሰፈር ፡
መጥቶ ፡ ሳለ ፤ ማነው ፡ እኔን ፡ የሚቋቋመኝ ፡ እያለ ፡ በሚያስፈራ ፡ ድምጽ ፡ እንደ ፡
ነጐድጓድ ፡ ሲያስገመግም ፡ ጎልያድን ፡ ሰማው ፤ ዳዊት ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ሳለ ፤ አንበሳና ፡
ነብር ፡ ገድሎ ፡ ነበርና ፡ እንዲሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ርዳታ ፡ ይህን ፡ ፍልስጥኤ
ማዊ ፡ እገድለዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ዐሰበ ።
፪ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከሳዖል ፡ ፊት ፡ ፈትለክ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ አረመኔ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡
ሊገጥመው ፤ ተንደረደረ ።
፫ ፤ ዳዊትም ፡ ሳዖል ፡ ያዋሰውን ፡ የንጉሥ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ተወና ፡ የረኛ ፡ ልብሱን ፡
ለብሶ ፡ ወደ ፡ መዋጊያው ፡ ስፍራ ፡ ሄደ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰይፍ ፡ አልታጠቀም ፡ ነበር ።
፬ ፤ ሁለቱም ፡ ተዋጊዎች ፡ ወደሚዋጉበት ፡ ስፍራ ፡ በተቃረቡ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡
ወገን ፡ የነበረው ፡ ዳዊት ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ በትር ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ደግሞ ፡ ወንጭ
ፉንና ፡ አምስት ፡ ድብልብል ፡ ድንጋዮች ፡ በኮረጆው ፡ ይዞ ፡ ነበር ።
፭ ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ወገን ፡ ኀይለኛው ፡ ሰውዬ ፡ ጎልያድ ፡ ጅንፎው ፡ አን
ዳች ፡ የሚያህል ፡ ጦሩን ፡ እየሰበቀና ፡ እያወዛወዘ ፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ እየተብ
ለጨለጨና ፡ እየበረቀ ፡ ወጣ ። ይኸው ፡ ኀይለኛው ፡ ሲናገር ፡ ድምጹ ፡ በላይ ፡ እን
ደሚያስገመግም ፡ ነጐድጓድ ፡ ነበር ።
፮ ፤ ወደ ፡ ዳዊት ፡ በንቀት ፡ እየተመለከተ ፡ ሊወጋው ፡ ዐሰበ ። ጦሩን ፡ እየቃጣበት ፡
ወደዚህ ፡ ቅረብ ፡ ሥጋህን ፡ የምሰጠው ፡ ላሞራ ፡ ነው ፡ አለው ።
፯ ፤ ጐልማሳው ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ ትንሽ ፡ ሰቅጠጥ ፡ ሳይል ፡ አንገትህን ፡ በጥሼ ፡ እጥለ
ዋለሁ ፡ ሬሳህንም ፡ ለዱር ፡ አራዊት ፡ አምዘገዝገዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የጀግንነት ፡ መልስ ፡
ለጎልያድ ፡ መለሰለት ። ይህም ፡ ፉከራና ፡ ማስፈራራት ፡ ጎልያድን ፡ አስቈጣውና ፡ ዳዊ
ትን ፡ ለመግደል ፡ ተቁነጠነጠ ።
፰ ፤ ጐልማሳው ፡ ዳዊት ፡ ጎልያድን ፡ ሊገጥመው ፡ ወደፊት ፡ እየሮጠ ፡ ከኮረጆው ፡ የለ
ዘበ ፡ ድንጋይ ፡ አወጣና ፡ በወንጭፉ ፡ ካሰናዳ ፡ በኋላ ፤ ርቀቱን ፡ መጥኖ ፡ ቢወንጭፍ ፡
የጎልያድን ፡ መኻል ፡ ግንባሩን ፡ ነጥርቆ ፡ ጣለው ።
፱ ፤ ደንጊያው ፡ ጠልቆ ፡ ገብቶ ፡ አንጐሉን ፡ ቢበጠብጠው ፡ ሬሳው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ተንዘራጋ ። የሚያብለጨልጭ ፡ ጥሩርና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ ዘፍ ፡ አለ ።
ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ዳዊት ፡ በገዛ ፡ ሰይፉ ፡ የጎልያድን ፡ አንገት ፡ ቈርጦ ፡ ወሰደ ። ፍል
ስጥኤማውያንም ፡ አርበኛቸው ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደኋላቸው ፡ ሸመጠጡ ።
፲ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተከታትለው ፡ አያሎችን ፡ በሰይፍ ፡ ጣሏቸው ። ዳዊ
ትም ፡ በቅባት ፡ የተጨማለቀ ፤ ለማየት ፡ የሚያስፈራ ፡ የጎልያድን ፡ ራስ ፡ ቈርጦ ፤
ጭብጭበውን ፡ ይዞ ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመለሰ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ዳዊት ፣ የተባለው ፣ ማነው ፣? ምንስ ፣ አደረገ ፣ ?
፪ ፤ ዳዊት ፣ ምን ፣ አድርጎ ፣ ነበር ፣? ምንስ ፣ ዐስቦ ፣ ነበር ፣ ?
፫ ፤ የዳዊትንና ፣ የጎልያድን ፣ ታሪክ ፣ ተናገር ።
፬ ፤ የጎልያድ ፣ ሞት ፣ በፍልስጥኤማውያን ፣ ላይ ፣ ያመጣው ፣ ምንድን ፣ ነው ።
፭ ፤ ዳዊት ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ክብረት ፣ አገኘ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፰ ፣ እስያ ፣ ይቀጥላል ።

### የዳዊት ፣ መንግሥና ፣ የሰሎሞን ፣ ጥበብ ።

፩ ፤ ዳዊት ፣ ጎልያድን ፣ ድል ፣ ካደረገ ፣ በኋላ ፣ ዝናው ፣ ዳር ፣ እስከ ፣ ዳር ፣ ተሰማ ለት ። በዚህ ፣ የተነሣ ፣ ሳዖል ፣ ተመቀኘውና ፣ ሊገድለው ፣ ተመኘ ። ነገር ፣ ግን ፣ የሳዖል ፣ ልጅ ፣ ዮናታን ፣ ዳዊትን ፣ ያለመጠን ይወደው ነበር ።

፪ ፤ ሳዖል ፣ በሕይወቱ ፣ እስካለ ፣ ድረስ ፣ ዳዊት ፣ የበለጠውን ፣ በስደት ፣ እንዲኖር ፣ ግድ ፣ ሆነበት ። ነገር ፣ ግን ፣ ሳዖል ፣ በነገሠ ፣ በ፳፬ ፣ ዓመት ፣ ከፍልስጥኤም ፣ ሰዎች ጋር ፣ ሲዋጋ ፣ በጊልቦአ ፣ ተራራ ፣ ወድቆ ፣ ቀረ ። ዮናታንም ፣ ያንለት ፣ በጦርነቱ ፣ ውስጥ ፣ እዚያው ፣ ሞተ ።

፫ ፤ ዳዊትም ፣ ይህን ፣ አደጋ ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ልብሱን ፣ እየቀደደ ፣ ያለመጠን ፣ አዝኖ ፣ አለቀሰ ። ሳዖልና ፣ ዮናታን ፣ ከሞቱ ፣ በኋላ ፣ መንግሥቱን ፣ ወረሰ ። ገና ፣ አስቀ ድሞ ፣ የይሁዳ ፣ ሰዎች ፣ በላያቸው ፣ እንዲነግሥ ፣ ለንጉሥነት ፣ መርጠውት ፣ ነበ ርና ፣ አሁንም ፣ በላያችን ፣ ይነግሥ ፣ ዘንድ ፣ ይገባዋል እያሉ ፣ ተጨዋጨዋሁለት ።

፬ ፤ ዳዊት ፣ የዘመኑን ፣ እኩሌታ ፣ ያሳለፈው ፣ በጦርነት ፣ ነው ። ብዙ ፣ ድልም ፣ አግኝቷል ። ስመ ፣ ጥሩው ፣ የጀግና ፣ መሪ ፣ መሆኑ ፣ ስለ ፣ ታወቀለት ፣ ደስ ፣ ይለው ፣ ነበር ። በዙሪያው ፣ ያሉትን ፣ አያሎች ፣ ነገዶች ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ መን ግሥቱን ፣ ከፍ ፣ ወደ ፣ አለ ፣ ደረጃ ፣ አድርሶ ፣ በለታላቅ ፣ ኀይል ፣ አድርጎታል ፤ ደግሞ ፣ ለዘላዓለም ፣ የማይረሳ ፣ ሰላማዊ ፣ ዝና ፣ አገኘ ።

፭ ፤ ንጉሥ ፣ ዳዊት ፣ ከእስራኤል ፣ ልጆች ፣ በጣም ፣ ያማረ ፣ መዝሙር ፣ ዘማሪ ፣ ነበር ። በዘመኑ ሁሉ ፣ የርሱ ፣ መዝሙር ፣ የእግዚአብሔር ፣ ምስጋና ፣ ነበር ፤ ዳዊት ፣ ከሞተ ፣ ይኸው ፣ አሁን ፣ ሦስት ፣ ሺሕ ፣ ዓመት ፣ ሆነው ። እነሆ ፣ እስከ ዛሬ ፣ በርሱ ፣ መዝሙር ምእመናን ፣ ሁሉ ፣ እግዚአብሔርን ፣ ያመሰግኑበታል ።

፮ ፤ በኋላኛው ፣ ዘመኑ ፣ ዳዊት ፣ ስለ ፣ ልጁ ፣ ስለ ፣ አቤሴሎም ፣ መሸፈትና ፣ ማመፁ ታላቅ ፣ ኀዘን ፣ ደረሰበት ። ከመቼውም ፣ ይልቅ ፣ ያዘነው ፣ ልጁ ፣ አቤሴሎም ፣ በምስት ፣ ቀስት ፣ ተነድፎ ፣ በዛፍ ፣ ላይ ፣ በጠጕሩ ፣ ተንጠልጥሎ ፣ አግኝቶ ፣ ኢዮ አብ ፣ ስለ ፣ ገደለው ፣ ነው ።

፯ ፤ ዳዊት ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ አርጅቶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በቤተ ፡
መንግሥቱ ፡ ሞተ ፤ መንግሥቱንም ፡ ልጁ ፡ ሰሎሞን ፡ ወረሰ ። ሰሎሞንም ፡ መን
ግሥት ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ከሽምግልናው ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፤
በልጅነቱ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ነበር ።
፰ ፡ እንዴ ፡ ነገሠ ፡ ወዲያው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ ትንሽ ፡
ሕፃን ፡ ይዘው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ። ሁለቱም ፡ ሴቶች ፡ ሕፃኑን ፡ የኔ ፡ ነው ፡ የኔ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ በመባባል ፡ ተጣልተው ፡ አራሱን ፡ ልጅ ፡ የጋራ ፡ አድርገው ፡ ለመ
ከፈል ፡ ደረሱ ። ዳኛ ፡ ግን ፡ ሕፃኑ ፡ ለየትኛዪቱ ፡ እንዲሆን ፡ ለመፍቀድ ፡ አስቸ
ጋሪ ፡ ነገር ፡ ሆነ ።
፱ ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ሰይፍ ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ ባጠገቡ ፡ የቆመውን ፡ አዘዘው ፡ ያን
ጊዜውን ፡ የተሳለ ፡ ሰይፍ ፡ ይዞ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሕፃኑን ፡ ለሁለት ፡ ቢከ
ፈሉ ፡ ክርክራቸው ፡ ያልቃል ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ ከሁለት ፡ ከፈልና ፡ እያንዳዲቱ ፡
ግማሹን ፡ ይዛ ፡ ትሂድ ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ።
፲ ፤ ከሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ አንዲቱ ፡ በውነት ፡ የሕፃኑ ፡ እናት ፡ የነበረች ፤ የሚያስፈ
ራውን ፡ ሰይፍ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ጣረሞት ፡ ያዛት ። ወዲያው ፡ ልጁን ፡ አትን
ኩት ፡ ለዚች ፡ ክፉ ፡ ሴት ፡ ስጡዋትና ፡ እንዳለ ፡ ትውሰድ ፡ አይታረድብኝ ፡ በሕ
ይወት ፡ ይቁምና ፡ ልጅ ፡ ይሁናት ፡ አለች ። ያችኛዪቱ ፡ ግን ፡ ለሕፃኑ ፡ ሳት
ራራ ፡ ድርሻዬን ፡ ብቻ ፡ እፈልጋለሁና ፤ ግማሹን ፡ ታገኘሁ ፡ ይበቃኛል ፡ አለች።
፲፩ ፤ ሰሎሞን ፡ ይህን ፡ ፀሳብ ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ እውነተኛዪቱ ፡ የሕፃኑ ፡ እናት ፡
ለሕፃኑ ፡ በመራራትዋ ፡ ስለታወቀው ፡ አይታረድብኝ ፡ ላለችው ፡ ሕፃኑን ፡ ሰጣት ።
የሕፃኑም ፡ እናት ፡ እስዋ ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ነገሩን ፡ ጨረሰ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሳዖል ፡ ለምን ፡ ዳዊትን ፡ ተመቀኘው ፡ ? ሳዖል ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፪ ፤ ዮናታን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የዳዊት ፡ አኑዋንዋር ፡ እንዴት ፡ ኑሩዋል ፡?
ሳዖልና ፡ ዮናታንስ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፤?
፫ ፤ ሳዖል ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በዳዊት ፡ እንዴት ፡
ያለ ነገር ደረሰበት ፡ ?
፬ ፤ ዳዊት ፡ ከዕድሜው ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኑ
ዋንዋር ፡ አሳለፈው ፡ ?
የዕብራውያንን ፡ ነገድ ፡ ወደምን ፡ ደረጃ ፡ አደረሳቸው ፡ ?
አሸናፊ ፡ ከመባል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ የተሻለ ፡ ዝና ፡ አገኘ ፡ ?
፭ ፤ መዝሙራትን ፡ የደረሰ ፡ ማነው ፡ ?
ስለ ፡ መዝሙር ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
ዳዊት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ኖረ ፡ ?
፮ ፤ አቤሴሎም ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፯ ፤ ዳዊት ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ ? ዙፋኑን ፡ ማን ፡ ወረሰ ፡ ?
ሰሎሞን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የሕፃኑን ፡ ታሪክ ፡ ንገረን ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሠራትና ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ሰሎሞንን ፡ እንደ ፡ ጐበኘች ።

፩ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ነገደ ፡ እስራኤልን ፡ በሀብትም ፣ በኀይልም ፡ ከፍ ፡ ወዳለ ፡ ደረጃ ፡ ያደረሳቸው ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ነው ፡ ብያችኋለሁ ። ስለዚህ ፡ መንግሥታቸው ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ ፣ ወርቅና ፡ ብር ፡ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ የሚገኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሊሠራለት ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ይዘጋጅ ፡ ጀመር ።

፪ ፣ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ዋናው ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሠራት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲደረግ ፡ በተለይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታዘዘ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። እነሆ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ከግብፅ ፡ ተወጡ ፡ ፬፻፹ ፡ ዓመት ፡ እስኪሆናቸው ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያገለግሉበት ፡ አንድ ፡ መቅደስ ፡ አልሠሩም ።

፫ ፣ ሰሎሞን ፡ ከጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ኮንትራት ፡ ተዋዋለ ፣ ጥዱንና ፡ ዝግባውን ፡ ለሥራ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንዲሰጠው ፣ ሰሎሞንም ፡ በየዓመቱ ፡ ስንዴና ፡ ዘይት ፡ ለጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሁለቱም ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ ። በኢየሩሳሌም ፡ ሰሜን ፡ በሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ያለች ፡ ጢሮስ ፡ ታላቅ ፡ የንግድ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ። እርስዋም ፡ ቀድሞ ፡ በንግድ ፡ የታመነች ፣ የፊኒቅያ ፡ (ፊንቄ) ፡ ገንዘብ ፡ ናት ።

፬ ፣ ከጢሮስ ፡ በተገኘው ፡ ዕንጨትና ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ በተጠረበው ፡ ደንጊያ ፡ ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ። የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ግንብ ፡ ርዝመት ፣ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስንዝር ፡ ስፋቱ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፣ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍታው ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሆኖ ፡ ተመግቢያው ፡ ከፍታ ፡ ያለው ፡ መተላለፊያ ፡ ነበረው ። በዙሪያው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕንፃዎች ፡ እየሆኑ ፡ የተሠሩት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፣ ለነዚህም ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ዙሪያ ፡ ፈቀቅ ፡ እያሉ ፡ ተሠርተዋል ።

፭ ፣ ነገር ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ የቅዱስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሥራ ፡ ያሠራሩንና ፡ የጌጡን ፡ እጅግ ፡ አስገራሚነት ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጽሕፈት ፡ ለማስረዳት ፡ የማይቻል ፡ ነው ። ውስጡ ፡ የተሠራው ፡ በርከት ፡ ያለው ፡ ዋጋ ፡ በለው ፡ በከበረ ፡ ዕንጨት ፡ ነው ። በግንቡ ፡ ላይ ፡ የኪሩቤል ፡ ምስልና ፡ ሌላም ፡ ለማየት ፡ ያማረ ፡ ተቀርጾበታል ። ግንቡና ፡ ወለሉ ፡ በሚያስፈልገው ፡ ክፍል ፡ በወርቅ ፡ ተለብጦአል ።

፮ ፣ ለመቅደሱ ፡ የሚሆኑ ፡ መሠዊያዎች ፡ ገበቶች ፣ መቅረዞችና ፡ ስፍር ፣ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ብዙ ፡ ዕቃዎች ፡ አሉት ፣ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፡ ነበር ። ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ በታላቅ ፡ በከበረ ፡ ገንዘብ ፡ ማለት ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ መሠራቱን ፡ ያሳያል ።

፯ ፤ ይህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በተጀመረ ፡ በ፯ ፡ ዓመት ፡ ተጨረሰ ። ዓለም ፡ በተፈጠረ ፡
በሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ መጨረሱ ፡ ነው ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡
ዓመት ፡ ይቀድማል ። ይህም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠርቶ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ለማስ
መረቅ ብሎ ፡ ሰሎሞን ፡ የእስራኤልን ፡ አለቆችና ፡ ሽማግሎችን ፡ ከቡራኑን ፡
ሁሉ ፡ አስጠራቸው ። ካህናቱና ፡ ሌዋውያንም ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡
እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ የሰጠውን ፡ ሁለቱ ፡ ገበቶች ፡ ያሉበትን ፡ ታቦት ፡
ይዘው ፡ መጡ ።
፰ ፤ ታቦቱን ፡ ከቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ከወርቅ ፡ ከተሠሩት ፡ ከሁ
ለቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ክንፎች ፡ በታች ፡ አኖሩት ። ታቦቱ ፡ ገብቶ ፡ ከመቀመጡ ፡ ወዲ
ያው ፡ ደመና ፡ መጥቶ ፡ መቅደሱን ፡ መላው ። በዚያ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ይህ ፡ ምልክት ፡ ነው ።
፱ ፤ ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ የጥበቡ ፡ ዝና ፡ ተስፋቶለት ፡ ነበ
ርና ፡ ስለዚህ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ዝናውን ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ከግዛትዋ ፡ ቀድሞ ፡
ሳባ ፡ ይባል ። ከነበረው ፡ ከዛሬው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተነሥታ ፡ ሰሎሞንን ፡ ለመጐብ
ኘት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣች ።
፲ ፤ የተጓዘችውም ፡ ብዙ ሠራዊት ፡ አስከትላ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ወርቅና ፤ የከ
በረ ፡ ዕንቈ ፤ የከበረም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፡ በግመል ፡ አስጭና ፡ ነበር ። ከሽቱው ፡
ጥራት ፡ የተነሣ ፡ በተጓዘችበት ፡ በረሃ ፡ ሁሉ ፡ ሽቱው ፡ ያውድ ፡ ነበር ።
፲፩ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ሆኖ ፡ በወርቅ ፡ ባጌጠ ፡
በታላቅ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሰሎሞንን ፡ አየችው ። የእግሮቹ ፡ ማረፊያ ፡
ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ። በዙፋኑ ፡ ዙሪያ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ሥዕለ ፡ አናብስት ፡
ነበሩ ። ንጉሡ ፡ በሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። ከንግሥተ ፡ ሳባም ፡
ጋር ፡ ሲነጋገሩ ፡ ከምትመለከተው ፡ ሁሉ ፡ የጥበቡንና ፡ የታላቅነቱን ፡ ነገር ፡ ታደ
ንቅ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ካየችው ፡ ሁሉ ፡ እኩሌታውን ፡ እንኳን ፡ እንዳልሰማች ፡
በግልጥ ፡ ተናገረች ፤ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ አይታው ፡ ቢሆን ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ የሚያስለቅስ ፡ ለውጥ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ትመለከት ፡ ነበር ። እውነተ
ኛውን ፡ አምላክ ፡ ከድቶ ፡ ለጣዖት ፡ ተንበረከከ ፡ ( ጣዖት ፡ አመለከ ፡ ) ይህ ፡
ጠቢብ ፡ ወደ ፡ ከፋት ፡ ተጣምሞ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ለአሕዛብ ፡ ጣዖት ፡
መስጊድ ፡ ሠራ ።
፲፪ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመንግሥቱ ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡
ሊከፍልበት ፡ ቍርጥ ፡ ዐሳብ ፡ አደረገ ።
፲፫ ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ እንዳሰበው ፡ ሰሎሞን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
ዐሥሩ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ በልጁ ፡ በሮብአም ፡ ላይ ፡ ዐመፁበት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ዳዊት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ወርቅና ፡ ብር ፡ በዕብራውያን ፡ ዘንድ ፤
እንዴት ፡ ኑሩዋል ፡ ?
፪ ፤ በሰሎሞን ፡ ዘንድ ፡ ዋና ፡ የሆነው ፡ ምንድን ፡ ኖርዋል ፡ ?
በማን ፡ ትእዛዝ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠራ ፡ ?
፫ ፤ ሰሎሞን ፡ ከጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ከኪራም ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ተዋውሎ ፡ ኑሩዋል ፡?
ፊኒቅያ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ? ኢየሩሳሌም ፡ ወይም ፡ ከነዓን ፡ በወዴት ፡
በኩል ፡ ነው ፡ ?
ከሚዴቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ?
መልስ ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ?
ጢሮስ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ኢየሩሳሌም ፡ ከባቢሎን ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይሆናል ፡ ?
፬ ፤ ከምሥር ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ይሆናል ፡ ?
ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የሠራው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?
መልስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሞሪያ ፡ በሚባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሠራው ።
የቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ስፋትና ፡ ሁኔታ ፡ ንገረኝ ።
፭ ፤ የውስጡን ፡ ሥራ ፡ ተናገር ።
፮ ፤ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ አገቡበት ፡ ?
፯ ፤ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ ተሠራ ፡ ?
የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመው ፡ ዓለም ፡ በተፈጠረ ፡ በስንተኛው ፡
ዓመት ፡ ነው ፡ ?
ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ተሠርቶ ፡ ካለቀ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡
ስንት ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ፡ ?
የቤተ ፡ መቅደስን ፡ መመረቅ ፡ ተናገር ።
፱ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆንች ፡ ? ከወዴት ፡ የመጣች ፡ ይመስልሃል ፡ ?
፲ ፤ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ አመጣጥዋን ፡ ንገረን ።
፲፪ ፤ በሰሎሞን ፡ ዘመን ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
ሰሎሞን ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ በማዘንበሉ ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ተከተለው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የአይሁድ ነገድ መድከም ።

፩ ፤ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ስለ ፡ ሸፈቱ ፡ ሮብአም ፡ በይሁዳና ፡ በብንያም ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡
ብቻ ፡ ነገሠ ፤ እነዚህም ፡ የይሁዳ ፡ መንግሥት ፡ ተባሉ ። የመንግሥቱን ፡ ታላ
ቁን ፡ ክፍል ፡ ማጣቱ ፡ አንሶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሌላ ፡ መከራ ፡ መጣበት ። ሺሻክ ፡
የምሥር ፡ ንጉሥ ፡ ሊዋጋው ፡ ተነሣበትና ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ ይዞ ፡ የቤት ፡ መቅ
ደሱን ፡ መዝገብና ፡ ሕዝቡንም ፡ ጥርግርግ ፡ አድርጎ ፡ ወሰደው ።
፪ ፤ ከሮብአም ፡ አፈትልከው ፡ የሸፈቱ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡
ቀን ፡ ጀምረው ፡ ለራሳቸው ፡ ንጉሣቸውን ፡ መርጠው ፡ አነገሡ ። አገሩም ፡ የእ
ስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ተባለ ። ከዚህም ፡ ከነገሡት ፡ የሚበዙት ፡ ጣዖት ፡ የሚ
ያመልኩ ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ቤተ ፡ መንግሥታቸውና ፡ ዋና ፡ ከተማ
ቸው ፡ ሰማርያ ፡ ይባላል ።
፫ ፤ የእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ከይሁዳ ፡ መንግሥት ፡ በተለየ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡
አምሳ ፡ ዓመት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ስልምናሶር ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አደረገውና ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንደባርያ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወሰዳቸው ። ከነሱም ፡
የሚበዙት ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ አልተመለሱም ።
፬ ፤ የይሁዳና ፡ የብንያም ፡ ነገድ ፡ ግን ፡ በከነዓን ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አይሁድ ፡ የሚባሉት ፡
እነርሱ ፡ ናቸው ። ቤተ ፡ መንግሥታቸውና ፡ የሚኖሩበተ ፡ ከተማቸው ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ነው ። ከአይሁድ ፡ ነገሥታት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ደጎች ፡ ነበሩ ። የሚበዙት ፡ ግን ፡
በኀጢአታቸውና ፡ ጣዖት ፡ በማምለካቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቀየሙ ።
፭ ፤ ነገደ ፡ አይሁድ ፡ ሲባሉ ፡ ሁሉም ፡ ጠማሞች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡
ወረደባቸው ። ፮፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ናቡከደነፆር ፡ የባቢሎን ፡
ንጉሥ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያዛትና ፡ (ወሰዳት ፡) ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ በዘበዘ ፡ ከሕዝ
ቡም ፡ ታላላቁን ፡ ማርኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዳቸው ።
፮ ፤ በ፭፻፹፮ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሴዴቅያስ ፡ ንጉሥ ፡ በነበረ ፡
ጊዜ ፡ ናቡከደነፆር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ወሰዳት ። የሱ ፡ ደጃዝማች ፡ የከተ
ማውን ፡ ቅጽር ፡ እየናደ ፡ አፈረሰው ። አንድ ፡ ነገር ፡ ሳይጠፋ ፡ የተገኘ ፡ አል
ነበረም ። አይሁድ ፡ ምርኮኞች ፡ ሆነው ፡ በባቢሎን ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጡ ።
፯ ፤ ቂሮስ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ባቢሎንን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በያዛት ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡
ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ስለ ፡ ፈቀደላቸው ፡ ቤተ ፡ መቅደሳቸውን ፡
ሠርተው ፡ የጥንት ፡ አምልኮዋቸውን ፡ መለሱ ። እስከ ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡
ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሕዝቡ ፡ ከፋርስ ፡
ንጉሥ ፡ በታች ፡ ሆነው ፡ ኖሩ ።

፰ ፤ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለመውሰድ ፡ ዐስቦ ፡ ሠራዊቱን ፡ አስከትቶ ፡ ሲመጣ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖውን ፡ ለብሶ ፤ የተማሩትን ፡ ሌዋውያንንና ፡ ሕዝቡን ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ተቀበለው ፡ እስክንድር ፤ ሁኔታቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተስማማና ፡ ለከተማዪቱም ፡ ራራላት ።

፱ ፤ ይህ ፡ በሆነ ፡ በሁለተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ግብፃውያን ፡ የአይሁድን ፡ መንግሥት ፡ ወረሩት ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሶርያውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሕዝቡን ፡ በባርነት ፡ እየገዙ ፡ እጅግ ፡ ሥቃይ ፡ አስቀበሉዋቸው ።

፲ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፻፷፯ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የነበረ ፡ ይሁዳ ፡ መቃቢውስ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ቈራጥ ፡ ጀግና ፡ የሶርያን ፡ ሰዎች ፡ እያከለበለበ ፡ ከአገሩ ፡ አስወጣቸው ። ይህንንም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የአይሁድን ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለሁ ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቸኩሎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲገሠግሥ ፡ ተሠረገላው ፡ ወድቆ ፡ሞተ ።

፲፩ ፤ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ መቃቢዎስ ፡ ዘሮች ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ወሰዱና ፡ የአይሁድ ፡ ነገሥታት ፡ ለመሆን ፡ በቁ ። አገሩ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ በፖምፔ ፡ ተገዛ ፡ ርሱም ፡ ስሙ የተጠራ ፡ የሮም ፡ ጀኔራል ፡ ነበር ። በኋላም ፡ መንግሥቱን ፡ አንቲፓትር ፡ ለተባለ ፡ ለኤዶም ፡ ሰው ፡ ሰጠው ።

፲፪ ፤ ፴፯ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ የአንቲፓትር ፡ ልጅ ፡ ሄሮድስ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲሆን ፡ የሮም ፡ አማካሪ ፡ ዐወጀለት ። በቤተ ፡ ልሔም ፡ አውራጃ ፡ የተገኙ ፡ ሕፃናት ፡ ሁሉ ፡ እንዲገደሉ ፡ ያዘዘ ፡ ይኸው ፡ ሄሮድስ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ማለቱ ፡ ሕፃኑ ፡ ኢየሱስ ፡ በዚያ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቶ ፡ አብሮ ፡ እንዲገደል ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሆነ ፡ የተመሰገነው ፡ ሕፃን ፡ ኢየሱስ የሚወለድበት ፡ ጊዜ ፡ ተቃርቦ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

ሮብአም ፡ ማን ፡ ኑሩዋል ፡ ?

፩ ፤ በርሱ ፡ ዘመን ፡ ከሁለት ፡ የተከፈለው ፡ የነገደ ፡ ዕብራውያን ፡ መንግሥት ፡ ማንና ፡ ማን ፡ ተባለ ፡ ?

ለዐመፁት ፡ ለዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ ተሰጣቸው ፡ ምን ፡ ተባሉ ፡ ?

ለሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ምን ፡ ስም ፡ ተሰጣቸው ፤ ምን ፡ ተባሉ ፡ ?

የእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ አገዛዝ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? ሺሻክ ፡ ማነው ፡ ?

፪ ፤ ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ተከነዓን ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ኑረዋል ፡ ?

የይሁዳ ፡ መንግሥት ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ኑሩዋል ፡ ?

የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

መኖሪያቸው ፡ ወዴት ፡ ኖሮአል ፡ ?

ሰማርያ ፡ በየት ፡ ወገን ፡ ነው ፡? ከኢየሩሳሌም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡?
መልስ ፡ አርባ ፡ ማይል ፡ ይርቃል ።

፫ ፤ ስልምናሶር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፬ ፤ አሁን ፡ የይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፤ ?

፭ ፤ ዋናው ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ነገደ ፡ አይሁድ ፡ እዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
ናቡከደነፆር ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፮ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ ተማርከው ፡ በባቢሎን ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ቈዩ ፡ ?

፯ ፤ ቂሮስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡? አይሁድ ፡ ተምርኮ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
ሕዝቡ ፡ በፋርስ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ነጻነት ፡ አግኝተው ፡ ኑረዋል ፡ ?

፰ ፤ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፱ ፤ ከእስክንድር ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፲ ፤ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ መቃቢያስ ፡ ተናገር ። ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
ሶርያ ፡ ተከነዓን ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?

፲፩ ፤ የይሁዳ ፡ መቃቢያስ ፡ ትውልድ ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ ? ፖምፔ ፡ ማነው ፡ ?
ይሁዳን ፡ እንዲገዛ ፡ ማንን ፡ ሾመ ፡ ?

፲፪ ፤ ሄሮድስ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲሆን ፡ የሮም ፡ አማከሮች ፡
የሾሙት ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
ስለ ፡ ሄሮድስ ፡ ተናገር ። ምን ፡ አደረገ ፡ ?

<u>ምዕራፍ ፡ ሸ፫ ፤ እስያ ፡ ይቀጥላል ።</u>

<u>የዕብራውያን ፡ ነቢያት ።</u>

፩ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ከዕብራውያን ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ተነሡት ፡ ሰዎች ፡ እስቲ ፡ ወደ ኋላዬ ፡ መለስ ፡ ብዬ ፡ ጥቂት ፡ ቃል ፡ ልንገራችሁ ። እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ ነቢያት ፡ ይባላሉ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አላቸው ። እግዚአብሔርም ፡ ወደፊት የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ እንዲናገሩ ፡ ዕውቀት ፡ ሰጥቶዋቸዋል ።

፪ ፤ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የታወቀ ፡ ነቢይ ፡ የነበረው ፡ ኤልያስ ፡ ነው ፡ (ይባላል) ስለ ርሱ ፡ ብዙ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ ተነግሮለታል ። በተለየ ፡ ስፍራ ፡ በብሕትውና ፡ ሲኖር ፡ ምግቡን ፡ ቁሮች ፡ ያመላልሱለት ፡ ነበር ። የአንዲት ፡ ባልቴት ፡ ልጅ ፡ ከሞት ፡ አድኖአል ።

፫፤ በከፋው ፡ ንጉሥ ፡ በአክአብ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተቀየመበት ፡ ተናግር
ዋል ። የተሸላለመችውን ፡ ንግሥት ፡ ኤልዛቤልን ፡ ውሾች ፡ ይግጡአታል ፡ ብሎ
ገና ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሯል ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አው
ርዶ ፡ ሁለቱን ፡ ሻምበሎች ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ እሳት አስበልቶአቸዋል ። የዮ
ርዳኖስን ፡ ወንዝ ፡ በመጠምጠሚያው ፡ ቢመታው ፡ ከሁለት ፡ ተከፍሎለት ፡ በደ
ረቅ ፡ ምድር ፡ ተሻግሮዋል ።
፬፤ በመጨረሻው ፡ መልእክቱን ፡ በምድር ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የእሳት ፡ ሠረገላና፤
የእሳት ፡ ፈረሶች ፡ መጥተው ፡ ኤልያስን ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ነጠቁት ።
፭፤ የኤልያስም ፡ መጠምጠሚያ ፡ ከእሳቱ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደቀና ፡
ጓደኛው ፡ ኤልሳዕ ፡ ቢያነሣው ፡ እርሱም ፡ እንደርሱ ፡ የታወቀ ፡ ነቢይ ፡ ሆነ ። ራሰ
በራ ፡ በመሆኑ ፡ ትንንሾች ፡ ሕፃናት ፡ ቢሥቁበት ፡ ረገማቸውና ፡ ሁለት ፡ የዱር ፡
አራዊት ፡ አስነሥቶ ፡ አርባ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆች ፡ አስፈጃቸው ።
፮፤ ኤልሳዕ ፡ ሙቶ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ በመቃብር ፡ ከቈየ፤ በኋላ ፡ ሌላ ሰው ፡
ሞተና ፡ ሬሳውን ፡ በኤልሳዕ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ቢያጋድሙት ፡ የነቢዩ ፡ ዐፅም ፡ ስለ
ነካው ፡ አዲሱ ፡ ሬሳ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ ተነሣና ፡ ሰው ፡ ሆነ ። (ሕያው ፡ ሆነ ።)
፯፤ ዮናስ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነቢይ ፡ ነበር ። ታላቅ ፡ ዓሣ ፡ ዋጠውና ፡ በባሕር ፡
ውስጥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ከደረ ፡ በኋላ ፡ ዓሣው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በደረቅ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ተፋው ።
ምንም ፡ አልሆነም ። ኢሳይያስም ፡ ደግሞ ፡ ነቢይ ፡ ነበር ፤ በእስራኤልና ፡ በይ
ሁዳ ፡ በዙሪያው ም ፡ ባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የሚመጣባቸውን ፡ መከራ ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ተናግሮአል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቅኤልና ፡ ኤርምያስ ፡ በኀጢአት ፡
ምክንያት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የሚመጣው ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ተገለጸ
ላቸው ፡ በኀዘን ፡ ድምፅ ጮኸዋል ።
፰፤ ብልጣሶር ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እንዲወድቅ ፡ ነቢዩ ፡ ዳንኤል ፡ አስቀድሞ ፡
ተናግሮአል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በባቢሎን ፡ ሳለ ፡ በንጉሡ ፡ በዳርዮስ ፡ ትእዛዝ ፡
ወደ ፡ አንበሳ ፡ ጕድጓድ ፤ ተጣላ ፡ በበነጋው ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ቢመለከት ፡
ምንም ፡ ሳይጐዳ ፡ ዳንኤልን ፡ አየው ።
፱፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳንኤልን ፡ ከአንበሳ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዲያወጡትና ፡ የዳንኤል ፡
ጠላቶች ፡ ወደ ፡ አንበሳ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዲጣሉ ፡ ንጉሡ ፡ ዳርዮስ ፡ አዘዘ ። እነዚህ
ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ተጥለው ፡ ገና ፡ ምድር ፡ ሳይነኩ ፡ አናብስቱ ፡
እየዘለሉ ፡ ቀልበው ፡ ሰባበሩዋቸው ።
፲፤ አያሌዎች ፡ ነቢያት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመን ፡ ተነሥተዋል ፤ ከነዚሁ ፡ አያሌዎቹ ፡
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተአምራት ፡ አሳይተዋል ። ይህንንም ፡ ኀይል ፡ የተቀበሉት ፡
ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ከአይሁድ ፡
ነገድ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ወየም ፡ ገዥ ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ የሚታይ ፡
ሰው ፡ ይገለጣል ፡ እያሉ ፡ ተናግረዋል ።

፲፩ ፤ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ እንዲመጣባቸው ፡ አስቀድመው ፡ ተናግረዋል ። መጽናኛ ፡ የሚሆናቸው ፡ ብቻ አንድ ፡ ነገር ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ የአይሁድን ፡ መንግሥት ፡ የሚያድስ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ይነሣና ፡ ግዛቱን ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ይመሠርታል ፡ የሚባል ፡ ትንቢት ፡ ነበራቸው ።

፲፪ ፤ ይህም ፡ ታላቅ ፡ ሁኔታ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሙሴ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብፅ ፡ ካወጣ በኋላ ፡ በ፲፭ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ይፈጸም ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበርና ፡ እንደንግሩ ፡ ተፈጸመ ። የቀጠሮው ፡ ወራት ፡ እንዳለፈ ፡ በሰማይ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በኩል ፡ ኮከብ ፡ ታየ ።

፲፫ ፤ ሦስት ፡ ጠቢባን ፡ ሰዎች ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ኮከቡን ፡ ከአዩት ፡ በኋላ ፡ እየመራቸውም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ መንደር ፡ አደረሳቸው ። ይኸውም ፡ አገር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፤ በዚያ ፡ ሕፃኑ ፡ ኢየሱስ ፡ በበረት ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ነቢያት ፡ ሥራቸው ፡ ምን ፡ ኑሩዋል ፡ ?
፪ ፤ ስለ ፡ ኤልያስ ፡ ምን ፡ ይነገራል ፡ ?
፫—፰ ፡ ኤልሳዕ ፤ ዮናስ ፤ ኢሳይያስ ፤ ሕዝቅኤል ፤ ኤርምያስ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፱ ፡ ዳንኤል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲ ፡ ስለ ፡ ነቢያት ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
ነቢያት ሁሉ ስለምን ፡ ተናገሩ ፡ ?
፲፩ ፤ ነቢያት ፡ ለሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ ምን ፡ እያሉ ፡ ያጽናኑዋቸው ፡ ኑሩዋል ፡ ?
፲፪ ፤ ክርስቶስ ፡ የተገለጠው ፡ ከሙሴ ፡ በኋላ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ ነው ፡ ?
በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የታየው ፡ የምን ፡ ኮከብ ፡ ነው ፡ ?
፲፫ ፤ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ምን ፡ ተደረገ ? ሰብአ ፡ ሰገል ፡ በበረት ፡ ምን ፡ አገኙ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### የኢየሱስ ፡ መወለድና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መጥፋት ።

፩ ፤ ለአይሁድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ተፈጸመ ። ይኸውም ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መምጣት ፡ ነው ። አንባቢዎች ፡ ሆይ ፡ በዚች ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፌ ፡ የዚህን ፡ የአምላካዊ ፡ ሰውነት ፡ ታሪክ ልትርከላችሁ ፡ አልችልም ።

፪ ፤ አይሁድ ፡ የምድራዊ ባለሥልጣን ፡ መስሉዋቸው ፡ በናፍቆት ፡ ዐይን ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር ። ብቻውን ፡ የሆነ ፡ የዋሁን ፡ ኢየሱስን ፡ ልብ ፡ አድርገው ፡ በተ

መለከቱት ፡ ጊዜ ፡ ናቁት ፤ ጠሉትም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ መሲሕ ፡ መሆኑን ፡ በግ
ልጽ ፡ ከተናገረ ፡ ጀምሮ ፡ ሊገድሉት ፡ ዐሰቡ ።
፫ ፡ በጲላጦስ ፡ ችሎት ፡ ፊት ፡ አቀረቡት ፤ ይህ ፡ ጲላጦስ ፡ ከሮማውያን ፡ ተሾሞ ፡
የይሁዳ ፡ ገዢ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበትና ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡
በሁለት ፡ ሌቦች ፡ መኻከል ፡ ተሰቀለ ። እርሱም ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በመቃብር ፡
ከቈየ ፡ በኋላ ፡ ከመቃብር ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ።
፬ ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡
ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በከነዓን ፡ አገርና ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ወንጌልን ፡ ለማ
ስተማር ፡ ወጡ ። ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሠራና ፡ ሥራውም ፡
ይከናወንለት ፡ የነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ነው ።
፭ ፤ በጳለስቲና ፤ በሶርያ ፤ በአስያሚኖር ፡ በግሪክ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ዞሮአል ።
በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ሊመረመር ፡ ከሌሎች ፡ እስረኞች ፡ ጋር ፡ ታስሮ ፡
በሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሄደ ።
፮ ፤ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ሲጓዝ ፡ ሳለ ፡ ማልታ ፡ ከምትባል ፡ ደሴት ፡ ሲደርስ ፡ ከጽኑ ፡
ማዕበል ፡ የተነሣ ፡ መርከቡ ፡ መሬት ፡ ነካና ፡ አልነቃነቅም ፡ አለ ። በኋላ ፡ ግን ፡
እንደገና ፡ ተጓዘና ፡ ሮም ፡ ደረሰ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፷፫ ፡
ዓመት ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ አገር ፡ እስረኛ ፡ ሆኖ ፡ እያል ፡ ቀን ፡ ቈየ ። ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ሊጠይቁት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የክርስትናን ፡ ትምህርት ፡ ያስተምራቸው ፡
ነበር ። ወዲያው ፡ ኔሮን ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ጳውሎስን ፡ አንገቱን ፡ አሰየፈው ።
፯ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ የወንጌልን ፡ ዘር ፡
ዘርተው ፡ ነበሩና ፡ ፍሬው ፡ ለመታየት ፡ ጀመረ ። በቅርብ ፡ መላው ፡ የሠለጠነው ፡
ዓለም ፡ የሮማውያንን ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የአረማውያን ፡
ሃይማኖት ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያለ ፡ ተወንጌል ፡ ፊት ፡ እያፈገፈገ ፡ ተወገደ ።
ክርስትናም ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ በመላ ፡ ኤውሮጳ ፡ ለመዘርጋት ፡ በቃ ።
፰ ፡ ከክርስቶስ ፡ ስቅለት ፡ አስቀድሞ ፡ አይሁድ ፡ ፈጽመው ፡ ለሮም ፡ መንግሥት ፡
ተገዝተው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከጌታችን ፡ ስቅለት ፡ በኋላ ፡ በአርባ ፡ ዓመቱ ፡
በገዦቻቸው ፡ ላይ ፡ ሸፈቱ ።
፱ ፤ ጥጦስ ፡ የሮም ፡ ሹም ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ ለመከበብ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ገሠገሠና ፡
ታላቅ ፡ የሚያስፈራ ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ። ባላገሮቹ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ እንዲሆኑ ፡
ተከበቡ ። ወዲያው ፡ ከተማው ፡ ተራበ ፤ አንዲት ፡ አይሁዳዊት ፡ ሴት ፡ ረኃብ ፡
ቢሞርዳት ፡ ልጅዋን ፡ በላችው ። ጥጦስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተናደደና ፡ የአይ
ሁድን ፡ ሕዝብ ፡ ዘር ፡ ለማጥፋት ፡ ማለ ። በዚያ ፡ በሚያስፈራ ፡ መከበብ ፡ ከመቶ ፡
ሺሕ ፡ የሚበዙ ፡ አይሁድ ፡ ተገደሉ ።
፲ ፤ ወዲያው ፡ ሌሊቱን ፡ ከተማው ፡ ተያዘና ፡ በእሳት ፡ ተቃጠለ ። ቤተ ፡ መቅደሱም ፡
በእሳቱ ፡ ነበልባል ፡ ተያያዘ ። ኢየሩሳሌም ፡ ተሠርቶበት ፡ በነበረው ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡

የእሳቱ ፡ ነበልባልና ፡ ወላፈን ፡ ሲምዘገዘግ ፡ ፀልከና ፡ የወጣበት ፡ ይመስል ፡ ነበር ። የታረዱት ፡ ባላገሮች ፡ ደም ፡ በሚቃጠለው ፡ እሳት ፡ ይፈላ ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ዘጠና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ አይሁድ ፡ ተማረኩ ። እኩሌቶቹም ፡ እንደባሪያ ፡ ተሸጡ ። ሌሎችም ፡ ምግብ ፡ እንዲሆኑ ፡ ለአራዊት ፡ ተወረወሩ ። በኢየሩሳሌም ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ቀርተው ፡ ስላ ፡ ነበሩ ፡ ከከተማው ፡ ትንሹ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተሠራ ። ያንንም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አድሪያን ፡ የተባለ ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ አጠፋው ። ግን ቡንና ፡ ቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ደልድሎ ፡ ከምድር ፡ ጋር ፡ አስተካከለውና ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ጨው ፡ ዘራበት ።

፲፪ ፤ አይሁድም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተበተኑ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሆን ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፡ ተነግሮ ፡ ነበር ። አሁን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓለም ፡ የሚገኙት ፡ አይሁድ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ። እስከ ፡ አሁን ፡ የጥንት ፡ ልማዳቸውንና ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዳጠበቁ ፡ ናቸው ። የኢየሩሳሌም ፡ ግማሹ ፡ ክፍል ፡ ታድሶአል ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የአሁኑ ፡ በጌታችን ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ ልዩነት ፡ አለው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ የታየው ፡ ምንድነው ፡ ?
ክርስቶስ ፡ ከተወለደ ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ሆነ ፡ ?
ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ በኋላ ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ ክርስቶስ ፡ ተገለጸ ፡ ?
የጥፋት ፡ ውሃ ፡ ካለፈ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዓመት ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፤ አይሁድ ፡ ክርስቶስን ፡ በምን ፡ ሀሳብ ፡ ተቀበሉት ፡ ?

፫ ፤ ጲላጦስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ስለ ፡ ሰቀሉት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፬ ፤ የክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጌታቸው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
ጳውሎስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፭ ፤ ጳውሎስ ፡ የትኞቹን ፡ አገሮች ፡ጐበኘ ፡ ? እስከ ፡ ወዴት ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮአል ።

፮ ፤ ጳውሎስ ፡ ይጓዝበት ፡ የነበረ ፡ መርከብ ፡ የተጋጨው ፡ ወዴት ፡ ሲደርስ ፡ ነው ፡ ? በሮም ፡ የደረሰው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ክርስትናን ለማን ፡ አስተማረ ፡ ? የመጨረሻ ፡ ዕድሉ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያት ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? የአሕዛብ ፡ ጣዖቶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ክርስትና ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፤ አይሁድ ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ የተገዙለት ፡ ለማን ፡ ነው ፡ ? ከክርስቶስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ባሣው ፡ ዓመት ፡ ምን ሆነ ?

፱ ፤ ጥጦስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መከበብ ፡ እስኪ ፡ ንገረን ፡ ?

፲ ፤ አድሪያን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? አየሁድ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፡ ምን ፡ ተነግሮ ፡ ኖሮአል ፡ ? ኢየሩሳሌም ፡ እንዴት ፡ ሆነች ።

## ፋ ር ስ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ቂሮስ ፡ ባቢሎንን ፡ ድል ፡ እንዳደረገና ፡ የቂሮስ ፡ ሞት ።

፩ ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በፊተኛው ፡ ክፍል ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ስለነበ
ረው ፡ ስለ ፡ አሶር ፡ መ ንግሥት ፡ ተናግሬአለሁ ። ይኸውም ፡ አገር ፡ ልብ ፡ ታደር
ጉት ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ጤግሮስና ፡ ኤፍራጥስ ፡ የሚባሉት ፡ ወንዞች ፡ በሚፈሱበት ፡
በኩል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ። ስፍራው ፡ በካርታ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡
ይታያል ። በዚህ ፡ አውራጃ ፡ አየሩ ፡ ሙቀታም ፤ መሬቱ ፡ ፍሬያም ፡ ነው ፤
በዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ በሚያስገርም ፡ ሆኖ ፡ ተራብቷል ።

፪ ፤ በዙሪያው ፡ ያሉት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በሕዝብ ፡ መልተው ፡ ወዲያው ፡ በቶሎ ፡ አያ
ሎቶ ፡ ነገዶችና ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሆኑ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አሶር ፡ ከነዚህ ፡ ነገዶች ፡
በሚበዙበት ፡ ላይ ፡ መንግሥቱን ፡ አስፋፍቶ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ የፋርስ ፡ መንግ
ሥት ፡ ኀይለኛ ፡ ሆነ ። አሶር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎችም ፡ አያሎች ፡ መንግሥቶ
ችና ፡ ታላላቅም ፡ ነገዶች ፡ ተገዙለት ።

፫ ፤ የፋርስ ፡ የ መጀ መሪያዎቹ ፡ ባላገሮች ፡ የሴም ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ የኤላም ፡ ዘሮች ፡
ናቸው ። ስላዚህ ፡ ኤላማውያን ፡ ይባላሉ ። ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡
ዓመት ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ከነበረው ፡ ታሪካቸው ፡ የታወቀው ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡
ነው ። ቂሮስ ፡ ታላቁ ፡ አሸናፊ ፡ በፋርስ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። አንዳንድ ፡
ባለ ታሪኮች ፡ ስለ ፡ ቂሮስ ፡ ሲናገሩ ፡ ብላህና ፡ የከበረ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ነገር ፡
ግን ፡ ከሌሎቹ ፡ ኣሸናፊዎች ፡ ከተባሉት ፡ የተሻለ ፡ አልነበረም ፡ ይላሉ ።

፬ ፤ ቂሮስ ፡ የግዛቱን ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ያሰፋ ፡ ጀ መር ። ሜዶን ፡ ጳርቲያ ፤ ሜሶጶታ
ሚያ ፡ አርማንያ ፡ ሶርያ ፤ ከነዓን ፤ የዐረብም ፡ ክፍል ፡ ተገዙለት ። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡
የግዛቱ ፡ ክፍል ፡ አደረጋቸው ። ካላቆቹ ፡ አንዱ ፡ የአሶራውያንን ፡ ከተማ ፡ ባቢሎ
ንን ፡ ያዛኑ ፡ የዚች ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ቅጽር ፡ ወፍራምና ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ቁመቱ ፡ በጣም ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ከቶ ፡ ጠላት ፡ ሊንደው ፤ ወይም ፡ በላይ ፡ ዘሎ ፡ ለመውጣትና ፡
ለ መግባት ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የጠነከረ ፡ ስፍራ ፡ ለመውሰድ ፡
በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ኣሁን ፡ ባቢሎን ፡ መኻከል ፡ አቃንቶ ፡ የኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ እንዲሄድበት ፡
የወንዙን ፡ ውሃ ፡ መልሶ ፡ ውሃ ፡ የሄደበትን ፡ ለማድረቅ ፡ ቂሮስ ፡ የከተማውን ፡ ዙሪያ ፡
የጠነቀ ፡ ጕድጓድ ፡ ኣድርጎ ፡ አስማሰው ። ጕድጓዱን ፡ ካስማሰ ፡ በኋላ ፡ የወንዙን ፡
ውሃ ፡ ለመልቀቅ ፡ የሚመች ፡ ጊዜ ፡ እንኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ቈየ ።

፮ ፤ ቤላሻናር ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ አድርጎ ፡ ነበር ።
ከቀየራቸው ፡ ውጪ ፡ ጠላት ፡ ይመጣብናል ፡ ብለው ፡ ምንም ፡ ሳይጠረጥሩ ፡

ዘበኞቹና ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይበሉ ፡ ይጠጡ ፡ ነበሩ ። ፋርሶች ፡ ጊዜ ፡ አገኙና ፡ የጐ ድጓዱን ፡ ግንብ ፡ ናዱት ።

፯ ፡ የኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ውሃ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ በላያቸው ፡ አጠለቃቸው ። ቂሮስ ፡ ራሱ ፡ በፋርስ ፡ ጭፍሮች ፡ ፊት ፡ ነበር ። የወንዙ ፡ ውሃ ፡ በሄደበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ የረገጡት ፡ የጫማቸው ፡ እርግጫ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

፰ ፡ የንጉሡ ፡ ዘበኞች ፡ ሳያስቡት ፡ ተገደሉ ፡ ቤልሻጸር ፡ ከክቡራኑ ፡ ጋር ፡ በዳራሹ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ የልቅሶኛ ፡ የጦር ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፡ ለማምለጥ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ አለፈ ፡ ሁሉም ፡ በዚያው ፡ ዐረፋና ፡ (ታረዱና) ደማቸው ፡ ከበዓሉ ፡ ወይን ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ባቢሎን ፡ የተያዘ ፡ አሶርያም ፡ የፋርስ ፡ ክፍል ፡ ሆነ ።

፱ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቂሮስ ፡ በጀግኖቹ ፡ በሺቲያኖች ፡ ላይ ፡ ተነሣ ፡ (ዘመተባቸው) ፡ የነዚህም ፡ መኖሪያቸው ፡ በካስፒያን ፡ ባሕር ፡ በሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ንግሥታቸው ፡ ቶሚሪስ ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ አስከትታ ፡ ፋርሶችን ፡ ከፉኛ ፡ ስለ ፡ ገጠመቻቸው ፡ ቂሮስ ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ ተማረከ ። የሺቲያኖች ፡ ንግሥት ፡ ልጅ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሞቶ ፡ ነበርና ፡ የልጅዋን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ዐስባ ፡ ቂሮስን ፡ ግደሉ ፡ ብላ ፡ አሽከሮቹዋን ፡ አዘዘች ፡ እንዲሁ ፡ በሚያስፈራ ፡ አገዳደል ፡ ተገደለ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ መጀመሪያ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ ማነው ፡ ?
አሲሪያ ፡ ያለው ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
አየሩና ፡ መሬቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የሰው ፡ ዘር ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፡ ሰው ፡ እየበዛ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮአል ፡ ? አሲሪያና ፡ ፋርስ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? ፡ ፋርስ ፡ ተከነዓን ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
የዐረብ ፡ አገርና ፡ የካስቢያን ፡ ባሕር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ በፋርስ ፡ ደቡብ ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?

፫ ፡ የፋርስ ፡ የጥንቱ ፡ ባላገሮች ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
ቂሮስ ፡ በፋርስ ፡ ዙፋን ፡ የተቀመጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ፋርስ ፡ ተቂሮስ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ እንዴት ፡ ኖሮአል ? ፡ የቂሮስ ፡ አካ ሄድና ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፬ ፡ ቂሮስ ፡ ድል ፡ እያደረገ ፡ የያዛቸው ፡ አገሮች ፡ ማንና ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
ሜዲያ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ከፋርስ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
ፖርቲያ ፡ ሚሶጶታሚያ ፡ አርማንያ ፡ ሶርያ ፡ ከነዓን ፡ ዐረብ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ?
ባቢሎን - እንዴት ፡ እንደተያዘች ፡ አጥርተህ ፡ ንገረኝ ፡ ?

፳ ፤ የአሲሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ በመሆን ፡ ተፈጸመ ፡ ?
ሲቲያኖች ፡ የሚኖሩት ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ? ጠባያቸው ፡ እን ዴት ፡ ይሆን ፡ ? ቂሮስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፮ ፡ እስያ ።

### ጸለ ፡ ካምቢሲስ ፡ መንግሥ ።

፩ ፤ የቂሮስ ፡ ልጅ ፡ ካምቢሲስ ፡ ካባቱ ፡ ይልቅ ፡ አብልጦ ፡ የከፋ ፡ ሰው ፡ ይመ ስላል ። ወይን ፡ ለመጠጣት ፡ እጅግ ፡ የጐመጀ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ጵሬክሳስጵስ ፤ የተባለ ፡ የንጉሥ ፡ ባለሙዋል ፡ ወይን ፡ ጤናህን ፡ ይጐዳዋል ፤ ሰውነትህንም ፡ ያደክምሃል ፡ ብሎ ፡ ቢመክረው ፤ ይህን ፡ ምክር ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ካምቢሲስ ፡ ወይን ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ አያሎች ፡ ማብረጃዎች ፡ ጨለጠና ፡ ዐይኔን ፡ የሚያፈዘው ፤ እጄ ንም ፡ የሚያንቀጠቅጠው ፤ ወይን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስኪ ፡ አያለሁ ፡ አለ ።

፪ ፤ ይህን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ቀስትና ፡ ፍላፃ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ የጵሬክሳስጵስን ፡ ልጅ ሒድና ፡ ራቅ ፡ ብለህ ፡ ካዳርሹ ፡ መጨረሻ ፡ ቁም ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ። ብላቴናውም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ የብላቴናው ፡ አባት ፡ እዚያው ፡ ቁሞ ፡ እየተመለከተ ፡ ጨከኙ ፡ ካምቢሲስ ፡ ወደዚያ ልጅ ፡ አነጣጥሮ ፡ ፍላፃውን ፡ ቢስብ ፡ በደረቱ ፡ ሰካበት ።

፫ ፤ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የምታነቡ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ የሚያስፈራ ፡ ታሪክ ፡ ስነግራችሁ ፡ በጣም ፡ አዝናለሁ ፤ ውሸት ፡ ኖሮ ፡ ቢሆን ፡ ባልተናገርሁም ፡ ነበር ። በነዚህ ፡ ታሪኮች ፡ መልካምና ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንማራለን ። ነገሥ ታት ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ ደስታ ፡ የሌላቸው ፡ ክፎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያስተምረናል ።

፬ ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በማይደረግበት ፡ ዘመን ፡ መኖራችን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። የምነግራችሁን ፡ በየዘመኑ ፡ የሆነውን ፡ እስቲ ፡ እናስበው ፡ ! በዚያው ፡ ዘመን ፡ ሕዝብ ፡ ለንጉሦቻቸው ፡ እንደመጫወቻና ፡ ሊያገለግሉዋቸውም ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ ይታሰብ ፡ ነበር ። ሌላው ፡ እንደ ፡ አደረገለት ፡ እንዲሁ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ለሌላው ፡ ቢያደርግለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑን ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተማረን ፡ ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ወዲህ ፡ መጥቶ ፡ ነው ።

፭ ፤ እውነት ፡ ነው ። በብዙ ፡ አገሮች ፡ ይልቁንም ፡ በእስያ ፡ የክርስቶስ ፡ አምላ ካዊ ፡ ሕግ ፡ አልታወቀም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተካምቢሲስ ፡ ዘመን ፡ ይልቅ ፡ ነገሥ ታት ፡ ዛሬ ፡ እጅግ ፡ መልካሞች ፡ ሆነዋል ።

፮ ፤ ነገሬን ፡ ወደፊት ፡ እቀጥላለሁ ። ካምቢሲስ ፡ ተግብጾች ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ አድርጎ ፡ ተከተሞቻቸው ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በከበበ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ስፍራ ፡ ለመያዝ ፡ አንድ ፡ የብልጠት ፡ መንገድ ፡ አገኙ ፡ ግብፆች ፡ ውሾችንና ፡ ድመቶችን ፡ ቅዱሶች ፡ እን ስሶች ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ አማልክቶቻቸው ፡ አድርገው ፡ ያመልኩዋ

ቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ያንን ፡ ከንቱ ፡ አምልኮታቸውን ፡ ካምቢሲስ ፡ ተምንም ሳይቈጥረው ፡ ባገሩ ፡ የሚገኙትን ፡ ውሾችና ፡ ድመቶች ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበና ፡ ከጦር ፡ ግምባር ፡ አስቀደማቸው ።

፬ ፤ ግብፃችም ፡ አማልክት ፡ የሚሉዋቸውን ፡ በጦር ፡ ፊት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የሚገድሉባቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፍላፃ ፡ ለመወርወር ፡ ፈሩ ። ፋርሶች ፡ ግን ፡ ውሾችንና ፡ ድመቶችን ፡ እያስጮሁ ፡ ወደፊት ፡ ገፉ ፤ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ፋርሶች ፡ ያለአንዳች ፡ ጦርነት ፡ ከተማዪቱን ፡ ያዝዋት ።

፭ ፤ የግብፃች ፡ ዋናው ፡ ጣዖታቸው ፡ አፒስ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ኮርማ ፡ ነበራቸው ። ይህንኑ ፡ ቅዱስ ፡ ኮርማ ፡ ካምቢሲስ ፡ አረደና ፡ ሥጋውን ፡ ለወታደሮቹ ፡ ምሳ ፡ እንዲሆን ፡ ሰጣቸው ። ወዲያው ፡ ያንጊዜውን ፡ በድንገት ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ስለ ፡ ገደለ ፡ ለግብፃችም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነላቸው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ካምቢሲስ ፡ እዴት ፡ ሆነ ? ስለርሱ ፡ ምን ፡ ታሪክ ፡ ታሰማናለህ ፡ ?

፪ ፤ የጥንት ፡ ነገሥታትን ፡ የሚያሥቅ ፡ ታሪካቸውን ፡ በመስማት ፡ ምን ፡ ትምህርት ፡ እናገኝበታለን ፡ ?

፫ ፤ ከጥንት ፡ ዘመናት ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ምን ፡ ታስብ ፡ ኖሩአል ፡ ? ክርስቶስ ፡ ከነገረን ፡ ወዲህ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የክርስቶስ ፡ ሕግጋት ፡ ያልታወቁት ፡ በወዴት ፡ ነው ፡ ? አሁን ፡ ነገሥታት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፬ ፤ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ አንዱን ፡ የግብፅን ፡ ከተማ ፡ ካምቢሲስ ፡ ማረከው ?

፭ ፤ አፒስ ፡ የተባለው ፡ የግብፃች ፡ ጣዖት ፡ እንዴንት ፡ ሆነ ፡ ? ካምቢሲስ ፡ እንደምን ፡ ሞተ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ እስያ ፡ ይቀጥላል ።

### ዞርክስ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ዘመተ ።

፩ ፤ ዳርዮስ ፡ የሚባል ፡ ሌላ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ግፍኛ ፡ ገዢ ፡ ነበር ። ሲቲያኖችን ፡ ለመውጋት ፡ በዘመተ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ የሚሆኑ ፡ የአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ልጆች ፡ ከወታደሮቹ ፡ ጋር ፡ ሁነው ፡ በግድ ፡ እንዲዘምቱ ፡ አዘዘ ። ለሽማግሌው ፡ የነበሩት ፡ ልጆች ፡ እነዚሁ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ሽማግሌው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀረበና ፡ አንዱ ፡ እንኳ ፡ ይቅርልኝ ፡ እያለ ፡ ለመነው ።

፪ ፤ አርጅቻለሁና ፡ ደካማነኝ ፡ እኔ ፡ ሠርቼ ፡ ለማደር ፡ አልችልም ፡ ልጆቼን ፡ ሁሉ ፡ የወሰድክብኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በችጋር ፡ እሞታለሁ ፡ ቢለው ፡ ንጉሡ ፡ ዳርዮስ ፡

ያዘነለት ፡ እያስመሰለ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ሽማግሌ ፡ ነህና ፡ ሦስቱም ፡ ይቅሩልህ ፡ አለው ። ያንግዜውን ፡ ሦስቱም ፡ እንዲገደሉ ፡ አዘዘና ፡ ከተገደሉ ፡ በኋላ ፡ ሬሳቸውን ፡ እኒኸውልህ ፡ ብሎ ፡ ለሽማግሌው ፡ ሰጠው ።

፫ ፤ ወዲያው ፡ ዳርዮስ ፡ ግሪክን ፡ ለመውጋት ፡ ሲሰናዳ ፡ በድንገት ፡ ታሞ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ልጁ ፡ ዘርክስ ፡ በስፍራው ፡ ተተካ ። ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚሊዮን ፡ እኩሌታ ፡ የሚሆኑትን ፡ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ አደረገና ፡ ግሪክን ፡ ወረረ ።

፬ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሊሰበስብ ፡ የሚችል ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ኀይል ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ታምኑኛላችሁ ፤ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ እጅግ ፡ ሰፍቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘርክስ ፡ ሌሎችን ፡ አገሮች ፡ ሊሸንፍ ፡ ለመያዝ ፡ ይመኝ ፡ ነበር ። ዋና ፡ ከተማው ፡ ፐርሲፖሊስ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ እጅግ ፡ ለማየት ፡ ያማሩ ፡ ከተሞች ፡ ከተባሉት ፡ አንዱ ፡ ነው ።

፭ ፤ በዚህም ፡ ዘርክስ ፡ የሚታይ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነበረው ። ለቍጥር ፡ የሚያሳስት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የከበረ ፡ ደንጊያም ፡ ( ዕንቍ ፡ ) ነበረው ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ የትዕቢትና ፡ የኵራት ፡ መንፈስ ፡ መልቶት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከበውት ፡ እንዲህ ፡ የተሙዋላለት ፡ ጌታ ፡ ሳለ ፡ ገና ፡ በቃኝ ፡ አላለም ፡ ነበር ። ሌሎችን ፡ ነገዶች ፡ አልፎ ለመያዝ ፡ ይጣጣር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አከማቸ ፤ ይህንንም ፡ ማድረጉን ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ።

፮ ፤ ዘርክስ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡን ፡ በሚያሳልፍበት ፡ አኳያ ፡ አቶስ ፡ የሚባል ፡ ተራራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተመንገዱ ፡ ላይ ፡ ተወገድ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጻፈለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ተራራው ፡ አቶስ ፡ ተስፍራው ፡ ንቅንቅ ፡ አላለም ።

፯ ፤ ከእስያ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለማምጣት ፡ ከባሕር ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ሔልስፖንት ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ዘርክስ ፡ የጀልባ ፡ ድልድይ ፡ ሠራ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ድልድዩን ፡ ማዕበል ፡ ሰባበረው ። ከበሬታ ፡ ስለ ፡ አላደረገለት ፡ ዘርክስ ፡ ባሕሩ ፡ እንዲገረፍ ፡ አዘዘ ።

፰ ፤ ተከተማው ፡ የሚገባልጠው ፡ የግሪክ ፡ ክፍል ፡ ላዘርክስ ፡ ተገዛ ። ነገር ፡ ግን ፡ እስፓርታና ፡ አቴን ፡ አሻፈረን ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ ሞገዱ ። ምንም ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ጥቂቶች ፡ ሆነው ፡ ቢወጡ ፡ ከፋርሶች ፡ ይልቅ ፡ እነዚህ ፡ ጀግኖች ፡ ነበሩ ።

፱ ፤ ዘርክስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ቴርሞፕሊ ፡ በሚባል ፡ በባሕርና ፡ በተራራ ፡ መኻከል ፡ ባለ ፡ በአንድ ፡ ጠባብ ፡ ስፍራ ፡ ለማሳለፍ ፡ ስለ ፡ ፈለገ ፤ ሊዮዲናስ ፡ የተባለ የእስፓርቶች ፡ ንጉሥ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ አላሳልፍህም ፡ አለው ። ፋርሶች ፡ በዚያች ፡ ስፍራ ፡ ሰብረን ፡ እናልፋለን ፡ ብለው ፡ ሲከራከሩ ፡ ሰባ ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ከፋርስ ፡ ወገን ፡ ወደቀ ።

፲ ፤ በመጨረሻው ፡ ሊዮዳኔስ ፡ ፋርሶች ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይመለሱ ፡ ተረዳው ፤ የቀሩትን ፡ ወዲያ ፡ ሰደደና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ቴርሞፕሊ ፡ የተባለች

ውን ፡ ጠባቢቱን ፡ በር ፡ ያዛት ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ የፋርስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እንደ ጐርፍ ፡ ሆኖ ፡ ገፍቶ ፡ ወጣ ። የቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ሲታረዱ ፡ ከሦስቱ ፡ መቶ ፡ ወታደሮች ፡ ለወሬ ፡ ነጋሪ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ አምልጦ ፡ መጣ ።

፲፩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዘርስስ ፡ ድል ፡ አደረግሁ ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ አልቈየም ። መርከቦቹ ፡ ሳላሚስ ፡ ላይ ፡ የእግር ፡ ሠራዊቱም ፡ ፓላቲያ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ስለ ሆኑ ፡ በአንዲት ፡ ትንሽ ፡ የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ታንኳ ፡ ተጋብቶ ፡ በሔሌስፖንት ፡ ለማምለጥ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ፤ ባሕሩም ፡ በመገረፍ ፡ ፈንታ ፡ ከጀልባ ፡ የተሠራውን ፡ ድልድዩን ፡ ሰባበረበት ።

፲፪ ፡ ትዕቢተኛው ፡ ዘርስስ ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቈየም ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ገደሉት ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፬፻፹፭ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፫ ፡ የዘርስስ ፡ ታሪክ ፡ ከንቱ ፡ ክብር ፡ መፈለግንና ፡ ስንፍናን ፡ ያስተምረናል ። በአገሩ ፡ ተቀምጦ ፡ ሕዝቡን ፡ ደስ ፡ እያሰኘ ፡ መግዛት ፡ በቅቶት ፡ ቢሆን ፡ ለርሱ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡ የበለጠ ፡ ለማግኘት ፡ ስለ ፡ ተጋደለ ፡ በራሱና ፡ ሚሊዮን ፡ በሚሆኑ ፡ ሰዎቹ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አመጣባቸው ።

፲፬ ፡ በገንዘብ ፡ ብዛትና ፡ ኀይል ፡ በማግኘት ፡ ደስታ ፡ እንደማይገኝ ፡ አይተናልና ፡ በትሕትና ፡ አኳኋን ፡ የያዝነው ፡ ይበቃናል ፤ ያ ፡ ሁሉ ፡ ኵራቱና ፡ ትዕቢቱ ፤ ልዕልናውና ፡ ክብረቱ ፡ ዘርስስን ፡ እንኳ ፡ መሣቂያ ፡ አደረገው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ዳርዮስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? እስኪ ፡ የክፋቱን ፡ ታሪክ ፡ ተርክልን ፡ ?

፪ ፡ የዳርዮስ ፡ ተከታይ ፡ ማነው ፡ ? ግሪክን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ የዘርስስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይበዛ ፡ ኑሩአል ፡ ? ግሪክ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
መልስ ፡ በኤሮጳ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ከፋርስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ፡ ?
መልስ ፡ ፲፭ ፡ ማይልስ ፡ ይርቃል ። ከፋርስ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
መልስ ፡ በሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ በዘርስስ ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ፔርሴፖሊስ ፡ እንዴት ፡ ኖሮአል ፡ ? ከባቢሎን ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነበር ፡ ? ከኢየሩሳሌም ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?

፫ ፡ የዘርስስ ፡ ሀብትና ፡ ክብረት ፡ እንዴት ፡ ኖሯል ፡ ?

፬ ፡ ከታወቀው ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጠው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የማን ፡ ነው ፡ ? አቶስ ፡ ስለሚባለው ፡ ተራራ ፡ ንገር ።

፭ ፡ ስለ ፡ ሔሌስፖትን ፡ ምን ፡ ታውቃለህ ፡ ? ስለ ፡ ግሪክስ ፡ ?

፮ ፡ ስለ ፡ ቴርሞፔሊ ፡ ምን ፡ ትላላህ ፡ ?

፲ ፤ ስለ ፡ ሊዎኔዳስ፡ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
፲፩ ፤ ሳሚስና ፡ ፕላቲያ፡እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ዘርስስ ፡ እንደምን ፡ ተመለሰ ፡ ?
፲፪ ፤ የዘርስስ ፡ አሙዋሙዋት ፡ ? ይህ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? በዘር ስስ ፡ ዙፋን ፡ ማን ፡ ተቀመጠ ፡ ?
፲፫ ፤ የዘርክስ ፡ ታሪክ ፡ ምን፡ያስተምረናል፡ ? ምን ፡ ያህል፡ደስታ፡ኖሮታል፡? በራሱና ፡ በሌሎች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መከራ፡አመጣ ፡ ?
፲፬ ፤ በቃን ፡ የማንል ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ ? ምንድን ፡ እናስታውሳለን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፰ ፤ እስያ ።

### የፋርስ ፡ ጕዳይ ፡ እስከ ፡ ሳራሲን ፡ ድል ።

፩ ፤ ባንድ ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ዘርስስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት፡በፊት፡ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ፡ዓመት፡የመቄዶንያ፡ንጉሥ፡ታላቁ፡ እስክንድር ፡ ፋርስን ፡ ወረራት ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ሦስተኛው፡ ዳርዮስ ፡ ነበር ። እስክንድር ፡ ድል፡አደረገውና ፡ የገዛ ፡ ዜጎቹ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት፡ ሰዎች ፡ በወርቅ ፡ ሠንሰለት ፡ አስረው ፤ በተሸፈነ ፡ ጋሪ ፡ ውስጥ ፡ አግብተው፡ አስቀመጡት ።

፪ ፤ ዳርዮስን ፡ ገድለው ፡ መንግሥቱን ፡ ለመያዝ ፡ አሰቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳይታሰብ፡ በድንገት ፡ እስክንድር ፡ መጣና ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የዶለቱትን ፡ ሰዎች ፡ አባረ ራቸው ። ተነሥተው ፡ ሲሸሹ ፡ ዳርዮስን ፡ በቀስት ፡ ወግተው ፡ ገድለውት ፡ ሄዱ ።

፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፋርስ ፡ ቀድሞ ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ለነበሩ ፡ ለፓ ርቲያኖች ፡ ተገዛ ፡ የፓርቲያኖች ፡ ነገሥታት ፡ ፋርስን ፡ ቅርብ ፡ አምስት፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ገዝተውታል ። ፪፻፶ ፡ ተክርስትና ፡ በፊት ፡ አርታክሶርስ ፡ የተ ባለ ፡ የፋርስ ፡ ሰው ፡ ሸፈተና ፡ መንግሥቱን፡እጅ ፡ አድርጎ ፡ ነገሠ ።

፬ ፤ የርሱ ፡ ዘሮች ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ትውልድ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ። ከነዚ ህም ፡ በጣም ፡ የታወቀው ፡ ኮስሮስ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት፡ በኋላ ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በሮማውያን ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ ጦርነት፡ አደረገና ፡ በእስያ ፡ የነበረ ፡ ግዛታቸውን ፡ ሁሉ ፡ በረበረ ፤ ዘረፈ ።

፭ ፤ የርሱም ፡ ወራሽ ፡ እንደርሱ ፡ ኮስሮስ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ የተጠላ ፡ ሰው ፡ አባቱን ፡ እስኪሞት ድረስ ፡ አስደበደበው ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቂሮስ ፡ የተባለ፡የገዛ ፡ ልጁን ፡ አስነሣና ፡ ቅጣቱን ፡ አስቀበለው ። አባቱን ፡ ከዙፋኑ፡ ዘርጥጦ ፡ አውርዶ ፤ ወንድሞቹንም ፡ ሁሉ ፡ እሬቱ ፡ አረዳቸው ።

፮ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቂሮስ ፡ አባቱን፡ ወደ፡እስር፡ቤት፡ወረወረው።ሽማግሌውን፡ንጉሥ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ገድሎ ፡ እንዳያሳርፈው ፡ በሾለ ፡ ፍላፃ ፡ እየወጋ ፡ ሥቃይ ፡ አስቀበ ለው ። በመጨረሻው ፡ ኮስሮስ ፡ በታላቅ ፡ ፃዕር ፡ ነፍሱ ፡ ወጣ ።

፯ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲናገሩት ፡ ስቅጥጥ ፡ ያሰኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጨካኞች ፡ ሰዎች ፡ ኀይል ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እንዲሆኑ ፡ ለማወቅ ፡ ይህን ፡ ለሚያነቡ ፡ ለጉልማሶቻችን ፡ ያስፈልግ ፡ ይሆናል ። የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ በሚ ያስጠይፍና ፡ ለማየት ፡ በሚያሰቀጥጥ ፡ በደል ፡ ላይ ፡ እንዳንታይ ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይ ማኖት ፡ አስተምሮናልና ፡ የተመሰገንን ፡ እንሁን ።

፰ ፤ በ፮፻፴፪ ፡ ተክርስትና ፡ በፊት ፡ በዙፋን ፡ የተቀመጠ ፡ የፋርስ ፡ የመጨረሻው ፡ ንጉሥ ፡ ኢስዲጀርት ፡ ነው ። በርሱ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ከዐረቦች ፡ አገር ፡ ሳራሴን ፡ የተ ባሉ ፡ ጦረኞች ፡ ሕዝብ ፡ ፋርስን ፡ ወረሩና ፡ ድል ፡ አደረጉት ። ኢስዲጀርትም ፡ በጦርነቱ ፡ ሞተ ።

፱ ፤ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ፋርስ ፡ የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ሆነ ። በጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በተሠራችው ፡ እጅግ ፡ ባማረችው ፡ ባግዳድ ፡ በተባለችው ፡ ከተማ ፡ በሚ ቀመጠው ፡ ከሊፋ ፡ ይገዛ ፡ ጀመር ።

፲ ፤ ይህ ፡ የታወቀ ፡ ስፍራ ፡ በ፯፻፷፪ ፡ ተመሠረተ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። እጅግ ፡ የከበሩ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩበት ። አሁን ፡ ግን ፡ ፈርሶ አል ። አሁን ፡ ያለው ፡ ከተማ ፡ በጣም ፡ የተዋረደ ፡ ነው ። ከሌላም ፡ ይልቅ ፡ ያነሰ ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ ፋርስን ፡ የወረረው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ማነው ፡ ?
፪ ፤ ዳርዮስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ያሙዋሙዋቱ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ ከዳርዮስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ፋርስ ፡ ለማን ፡ ተገዛ ፡ ?
ለፓርትያ ፡ መንግሥት ፡ ፋርስ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ተገዛ ፡ ?
ፓርትያ ፡ ያለው ፡ ከፋርስ ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?
አለክሳንድር ፡ የነገሠው ፡ ምንጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፬ ፤ ትውልዱ ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ ታላቁ ፡ ኮስሮስ ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ምንስ ፡ አደረገ ፡ ?
የታላቁ ፡ ኮስሮስ ፡ ወራሽ ፡ ማነው ፡ ?
፮ ፤ ቂሮስ ፡ ያደረገው ፡ ክፋት ፡ ምንድነው ፡ ?
፯ ፤ የሰዎች ፡ አውሬነት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
በምን ፡ የተመሰገንን ፡ እንሆናለን ፡ ?
፰ ፤ ኢስዲጀርት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ በዙፋን ፡ ተቀመጠ ፡ ?
ስለ ፡ ርሱ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
በርሱ ፡ ዘመን ፡ ሳራሴኖች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
በምን ፡ ምክንያት ፡ ኢስዲጀርት ፡ ተገደለ ፡ ?

፱ ፤ ፋርስ ፣ የማን ፣ መንግሥት ፣ ክፍል ፣ ሆነ ፣ ?
እንደምን ፣ ተገዛ ፣ ?
የከሊፍ ፣ መኖሪያ ፣ ወዴት ፣ ነበር ፣ ?
፲ ፤ ስለ ፣ ባግዳድ ፣ ምን ፣ ትላለህ ፣ ?

## ም ዕ ራ ፍ ፣ ፳፱ ፣ እ ስ ያ ።

### የፋርስ፣የዛሬው፣ታሪክ ።

፩ ፤ ፲፪፻፶፰ ፣ ተክርስትና ፣ በፊት ፣ የሳራሴንን ፣ መንግሥት ፣ ታርታሮች ፣ ከፍለ ውት ፣ ነበር ። ፋርስ ፣ አያል ፣ ጊዜ ፣ በራሱ ፣ ተገዛ ። በኋላ ፣ ሶፊስ ፣ ወይም ፣ ሻህስ ፣ በተባሉ ፣ ገዢዎች ፣ ተገዛ ፤ ከነዚህ ፣ የፊተኛው ፣ እስማኤል ፣ ይባላል ። እርሱም ፣ ከሳራሴኖች ፣ ወገን ፣ ነው ። መንግሥቱን ፣ በኀይል ፣ ወሰደና ፣ ፳፫ ፣ ዓመት ፣ ነገሠ ።

፪ ፤ ከነዚህም ፣ የበለጠው ፣ ንጉሥ ፣ ሻህስ ፣ ከቱርኮች ፣ ጋር ፣ ተዋግቶ ፣ ብዙ ፣ ድል ፣ አግኝቷል ። በፋርስ ፣ ባሕር ፣ መግቢያ ፣ ካለው ፣ እርሙዝ ፣ ከተባለው ፣ ደሴት ፣ ፖርቱጋሎችን ፣ አስወጥቷቸዋል ።

፫ ፤ ከነዚህ ፣ ነገሥታት ፣ ወገን ፣ ደግ ፣ ተብሎ ፣ የተጠራው ፣ ሻህስ ፣ ውሴን ፣ ነበር ። እርሱም ፣ መጨረሻ ፣ ነው ። እጅግ ፣ የተከናወነለት ፣ ሰው ፣ አልነበረም ፤ ባ፲፮፻፺፬ ፣ ዓመት ፣ ነገሠ ። ውሴንና ፣ ዜጎቹ ፣ ብዙ ፣ ችግር ፣ አግኝቶአቸው ፣ ነበር ፣ ወዲያው ፣ ዙፋኑን ፣ አሳልፎ ፣ ለሌላ ፣ እንዲሰጥ ፣ ግድ ፣ ሆነበት ።

፬ ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ ዘውዱ ፣ ገና ፣ ከራሱ ፣ ላይ ፣ ሳይነሣ ፣ እስጳሀን ፣ በሚሉት ፣ በዋናው ፣ ከተማ ፣ መኻከል ፣ ባለው ፣ ጐዳና ፣ ላይ ፣ በእግሩ ፣ ሲሄድ ፣ ታየ ። ሕዝቡ ፣ ዙሪያውን ፣ ከበቡና ፣ እየተጋፉ ፣ እየተተራመሱ ፣ ሲያለቅሱ ፤ ርኅሩኁና ፣ አዛኙ ፣ ንጉሥ ፣ ያጽናናቸው ፣ ነበር ።

፭ ፤ እንግዲህ ፣ አላቸው ፣ ስሙ ፣ ማህሙድ ፣ የተባለው ፣ አዲሱ ፣ ንጉሥ ፣ ከኔ ፣ አብልጦ ፣ የሚወዳችሁ ፣ አይደለም ። ነገር ፣ ግን ፣ በመልካም ፣ አገዛዝ ፣ ይገዛችኋል ፣ ጠላቶቻችሁንም ፣ ተከላክሎ ፣ ይመልስላችኋል ፣ አለና ፣ ደኅና ፣ ሁኑ ፣ ብሎ ፣ ሕዝቡን ፣ አሰናበተ ።

፮ ፤ ባ፲፯፻፴፮ ፣ ዓመት ፣ ኩሊክህን ፣ የተባለ ፣ በፋርስ ፣ ዙፋን ፣ ተቀመጠ ። እርሱም ፣ ጨካኝና ፣ ስመ ፣ ጥሩ ፣ ጀግና ፣ ነው ። ፲፩ ፣ ዓመት ፣ ከነገሠ ፣ በኋላ ፣ በድንኳኑ ፣ ውስጥ ፣ ታረደ ።

፯ ፤ አሁን ፣ የፋርስ ፣ ዋናው ፣ ከተማ ፣ቴሔራን ፣ ይባላል ። ሌላ ፣ ደግሞ ፣ እጅግ ፣ ያማረ ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ በኢስጳሀን ፣ ተሠርቶአል ። ይህንንም ፣ «ያርባ ፣ ምሰሶ ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ » ይሉታል ። አርባው ፣ ምሰሶ ፣ እያንዳንዱ ፣ ከነጭ ፣ ዕብነ ፣

ጨረድ ፡ በተቀረጸ ፡ አንበሳ ፡ ተደግፎአል ። ሕንፃው ፡ በመላው ፡ በዕንቍ ፤ በብር ፤ በወርቅ ፡ በከበረ ፡ ደንጊያ ፡ የተሠራ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

፰ ፤ መስከረም ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ. ም. የሞተው ፡ የቀድሞ ፡ ንጉሣቸው ፡ ልጅ ፡ ናስርኤድ ፡ ዲን ፡ የተባለው ፡ የኋለኛው ፡ ንጉሣቸው ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ የሚታይ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ፤ የሳይንስ ፡ ታላቅ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ (ኮሌጅ ፡) አቆመ ። በታኅሣሥ ፡ ፲፰፻፹፫ ፤ ኤሌክትሪክ ፡ ቴሌግራፍ ወደ ፡ ግዛቱ ፡ እንዲገባ ፡ ተዋዋለ ።

፱ ፤ ጨዚህ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቸለል ፡ ተብሎ ፡ በቈየ ፡ አገር ፡ የሥልጣኔ ፡ ግንኙነት ፡ በጊዜው ፡ ሥራውን ፡ እንዲሠራ ፡ ትልቅ ፡ ተስፋ ፡ አለ ። የየሱስ ፡ ክርስቶስም፡ ሃይማኖት ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ በሙሐመድ ፡ ላይ ፡ ያሸንፋል ።

፲ ፤ ፋርስ ፡ አየሩ ፡ መልካም ፡ ነው ። አገሩ ፡ ሽታ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ዛፍና ፡ ቍጥቋጦ ፡ አበባም ፡ የመላበት ፡ አገር ፡ ነው ። ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ሰዎች ፡ ጦር፡ ፈላጊዎች ፡ አይደሉም ። መንግሥቱን ፡ ከታላቁና ፡ ከሰፊው ፡ ከዘርስስ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ስናመዛዝነው ፡ የዛሬው ፡ ትንሽ ፡ ነው ። የጥንት ፡ ዋና ፡ ከተማ፡ የነበረው ፡ ፔርሲፖሊ ፡ ዛሬ ፡ አንድ ፡ የፈረሰ ፡ ቁልል ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ቴሄራንና ፡ ኤስጳሀን ፡ የተባሉት ፡ ሁለቱ ፡ ዋኖች ፡ ከተሞች ፡ ከዛሬው ፡ ከተሞች፡ ጋር ፡ ይወዳደራሉ ።

፲፩ ፤ የነገርኋችሁ ፡ የፋርሶች ፡ ጠባይ ፡ ፈጽሞ ፡ ክፉ ፡ አይደለም ። ሕዝቡ ፡ መጽሐፍ፡ ማንበብና ፡ ታሪክ ፡ ማስተማር ፡ ይወዳሉ ፡ ቅኔአቸውም ፡ መልካም ፡ ነው ። የተፈጥሮ ፡ ውበትንና ፡ ቍንጅናን ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ። ዛሬ ፡ የፋርስ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናሉ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓመት ፡ የሳራሴኖች ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ፋርስ ፡ እንደምን ፡ ተገዛ ፡ ? እስማኤል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፪ ፤ ሻኽ ፡ አባስ ፡ ማነው ፡ ? በዙፋን ፡ የተቀመጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ምንስ ፡ አደረገ ፡ ?

፫ ፤ ሻኽ ፡ ሁሴን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፬ ፤ ዘውዱን ፡ ያስረከበበትን ፡ አኳኋን ፡ ተናገር ።

፭ ፤ ኩሊኽህን ፡ የነገሠው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
ሌላ ፡ ስም ፡ ኖሮታልን ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፮ ፤ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ መኖሪያውን ፡ ወዴት ፡ አደረገ ፡ ?
ስለ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተናገር ።

፯ ፤ የዛሬው ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
በዘመኑ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፱ ፡ በዚያ ፡ ተስፋ ፡ የሚደረገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ?
፲ ፡ ፋርስ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
መሬቱና ፡ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
አገሩ ፡ በዘርስስ ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ ስፋት ፡ ጨምሯልን ፡ ?
ስለ ፡ ፔርሴፖሊስ ፡ ስለ ፡ ቴሔራንና ፡ ኢስፐሃን ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
፲፩ ፡ የፋርሶች ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እንዴ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴ ፡ እስያ ።

### የቺን ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪክ ።

፩ ፡ የቺን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አሁንም ፡ ያለው ፡ ጥንት ፡ እንደ ነበረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በሰሜን ፡ በኩል ፡ ከእሲያቲክ ፡ ረሺያ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ተፓሲፊክ ፡ ወ ቅያኖስ ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ተቺን ፡ ባሕርና ፡ ተህንድ ፡ ይዋሰናል። ከምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከቲቤትና ፡ ከታርታሪ ፡ የሚለይበት ፡ ተራሮችና ፡ አሸዋ ፡ የበዛባቸው ፡ ምድረ ፡ በዳዎች ፡ አሉ ።

፪ ፡ መንግሥቱ ፡ ከጥንት ፡ የነበረ ፡ ነው ። ጥንታዊ ፡ መንግሥት ለመሆኑ ፡ የሚወዳደረው ፡ አይገኝም ፡ የዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ከዘመናችን ፡ ይጀምርና ፡ ወደ ኋላው ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይዘልቃል ። ጥንት ፡ ከመጀመሪያ ፡ የቺንን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረተው ፡ ሰው ፡ ፎሒ ፡ ይባላል ። አንዳንዶች ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ኖኅ ፡ ማለት ፡ ይመስላል ፡ ይላሉ ።

፫ ፡ ኻያ ፡ ሁለት ፡ የንጉሥ ፡ ተወላጆች ፡ ወይም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዘመዶች ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ እያከታተሉ ፡ ቺንን ፡ ገዝተዋል ። በተለይ ፡ የየአንዳንዱ ፡ ታሪክ ፡ ቢተረክ ፡ ምንም ፡ ቢያንስ ፡ ኻያ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ መጻሕፍት ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ በር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለመታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ሥራ ፡ የሠሩት ፡ ነገሥታት ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

፬ ፡ ከፎሒ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ አምሮባቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ምግባቸውን ፡ ለመፈለግ ፡ በደን ፡ ውስጥ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ይዞሩ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ የሚኖሩበት ፡ ቤት ፡ አልነበራቸውም ። ማንኛውንም ፡ እንስሳ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ወፍ ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ ደሙን ፡ ይጠጡታል ፤ ጠጕሩንም ፡ ላባውንም ፡ ባንድነት ፡ ይበሉታል ፡ ብሉው ፡ ቺኖች ፡ ያምናሉ ።

፭ ፡ እስከ ፡ ኮዝ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ቺኖች ፡ ነገሥታት ፡ እጅግ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ አላገኘንም ። ይህም ፡ ኮዝ ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። እርሱም ፡ አጥብቆ ፡ አደን ፡ ይወድ ፡ ነበር ። አድናለሁ ፡ እያለ ፡ በሩዝ ሰብል ፡ መኻከል ፡ እየጋለበ ፡ ብዙ ፡ ጥፋት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ባላገሮቹ ፡ የሩዝ ፡ ሰብላቸውን ፡ ሲያደባይባቸው ፡ ጊዜ ፡ ሊያጠፉት ፡ አስበው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መከሩበት ።

፭ ፤ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ የሚመላለስበት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ወንዝ ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ሕዝቡ ፡ ለንጉሡ ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ታንኳ ፡ አስ ናድተው ፡ አኑረው ፡ ነበር ። በቢንጋው ፡ ንጉሡ ፡ ሲያድን ፡ ቈይቶ ፡ ከሽከሮቹ ፡ ጋር ፡ መጣና ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ለመሻገር ፡ ወደ ፡ ታንኳው ፡ ገባ ።

፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ ለማጥፋት ፡ ታንኳው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በብልሀት ፡ የተሠራ ፡ ነበርና ፡ ከወንዙ ፡ መኻከል ፡ ሲደርስ ፡ ታንኳው ፡ ፍርስርስ ፡ አለና ፡ በታንኳው ፡ የገቡ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሰጠሙ ። ንጉሡ ፡ ከዝ ፡ እንዲህ ፡ ሰጥሞ ፡ ከዓሦች ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተቀላቀለ ፡ የዜጎች ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። ለማደን ፡ ብሎ ፡ በሩዝ ፡ ሰብል ፡ ውስጥ ፡ ዳግመኛ ፡ አልተመለሰም ።

፯ ፤ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነገሠ ፡ ቺንግ ፡ የተባለ ፡ ንጉሣቸው ፡ ግዛቱን ፡ ከታርታሮች ፡ ለማዳን ፡ ብሎ ፡ ታላቅ ፡ ግንብ ፡ ሠራ ። ይህ ፡ ግንብ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለ ። ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍታው ፡ ፵፰ ፡ ፊት ፡ ወፍረቱ ፡ ፲፰ ፡ ፊት ፡ ነው ። በተራ ራውና ፡ በጕድጓዳው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ርቀቱ ፡ ፲፭፻ ፡ ማይል ፡ ነው ።

፰ ፤ ችንግ ፡ ግንቡን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆኑ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። ከርሱ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ምንም ፡ መታሰቢያ ፡ እንዳይኖር ላቸው ፡ ማንኛውም ፡ ቀድሞ ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ እንዲቃጠል ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊዎችን ፡ ሁሉ ፡ አዘዘ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የታሪክ ፡ መጻፍ ፡ ልምድ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አሰበሰበና ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሊቃውንት ፡ በሕይወታ ቸው ፡ ሳሉ ፡ ከነነፍሳቸው ፡ አስቀበራቸው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የቺኖች ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ዳርቻው ፡ እስከ ፡ የት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ?
ከቲቤትና ፡ ከታርታሪ ፡ የሚለየው ፡ ምንድነው ፡ ?
ቺን ፡ ከፋርስ ፡ ወዴት ነው ፡ ?
ሂንዱስታንስ ፡ ? ሳይቤሪያስ ፡ ? የቢርማን ፡ መንግሥትስ ፡ ?

፪ ፤ የቺን ፡ መንግሥት ፡ ጥንታዊነቱንና ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ እንደኖረ ፡ ተናገር ።
ታሪኩ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይኼዳል ፡ ? ማነው ፡ የመሠረተው ፡ ?
የአንዳንዶች ፡ ጸሓፊዎች ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ የቺን ፡ ገዦች ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ አገዛዝ ፡ እንዴት ፡ ኖሯል ፡ ?

፬ ፤ ከሮሚ ፡ በፊት ፡ የሰው ፡ ኑሮ ፡ ለቺኖች ፡ ምን ፡ ይመስላቸው ፡ ኖሯል ፡ ?

፭ ፤ ኮስ ፡ የነበረ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ? ስለርሱ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?

፮ ፤ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ እንዳጠፋት ፡ ተናገር ።

፯ ፡ ንጉሡ ፡ ችንግ ፡ የነበረበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ስለ ፡ ታላቁ ፡ ግንብ ፡ ተናገር ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለ ፡ ወይ ፡ ?

፰ ፤ ስለ ፡ ሊቃውንቱና ፡ ስለ ፡ ታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ንጉሡ ፡ ችንግ ፡ ምን ትእዛዝ ሰጠ ፤ ?